ትምህርት አሥራ አራት

ኢሳይያስ 43–45

የመጀመሪያ ቀን **ኢሳይያስ 43**

«ምስጋናዬን እንዲናገሩ ለእኔ የፈጠርሁት ሕዝብ... » (ኢሳ. 43፡21)

1ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ይህ ጥቅስ እግዚአብሔር ሕዝቡ እንሆን ዘንድ እኛን ስለመረጠበት ምክንያት የሚያስተምረን ምንድን ነው? (ተመሳሳይ አሳብ ከኤፌ. 1፡6፥ 12፥ 14 ተመልከት።) ለ) ይህ ብዙዎቻችን ስለ ደኅንነታችን ከምናስበው የሚለየው እንዴት ነው? ሐ) ክርስቲያኖች በንግግራቸው ብቻ ሳይሆን በሕይወታቸውም ለእግዚአብሔር ክብርን የሚያመጡባቸውን መንገዶች ግለጽ (1ኛ ቆሮ. 10፡31 ተመልከት)። መ) እግዚአብሔር ስላደረገልህ ነገሮች ታመሰግነው ዘንድ አሁኑኑ ጊዜ ውሰድ።

በሕይወታችን ውስጥ የራስ ወዳድነት ምልክት ከሚታይባቸው መንገዶች አንዱ ሁኔታዎችን በሰብአዊ ዓይኖች በመመልከት የሕይወት ፈርጦች በእኛ ዙሪያ እንደሚሽከረከሩ ማሰባችን ነው። ውሳኔዎቻችን በአብዛኛው ለራሳችን፥ ለወዳጆቻችን ወይም ለዘመዶቻችን በሚጠቅሙ ጉዳዮች ላይ የሚያተኩሩ ከሆነ ራስ ወዳድነታችን በግልጽ ይታያል። እንዲሁም ደግሞ ስንጸልይ ሳለ እግዚአብሔርን ለባሕርዩና ለተግባሩ እያመሰገኑ በማምለክ ፈንታ ለራሳችን ወይም ለሌሎች ሰዎች አንዳንድ ነገሮችን እንዲያደርግ በመጠየቅ ጊዜያችንን የምናጠፋ ከሆነም ራስ ወዳድነታችንን እንገልጣለን። እንዲሁም ደግሞ ስለ ደኅንነታችን ስንናገር እግዚአብሔር ያደረገልንን ሳይሆን እኛ እግዚአብሔርን ስለመምረጣችን አጽንኦት ሰጥተን የምንናገር ከሆነም በሰብአዊነት ላይ ያተኮረ ማንነት እንዳለን እናሳያለን።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን ሕይወትን የሚመለከታት በመለኮታዊ እንጂ በሰብአዊ እይታ አይደለም። በመጽሐፍ ቅዱስ የአስፈላጊው ነገር ማዕከል እግዚአብሔር እንጂ ሰው አይደለም። አብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የእግዚአብሔርን ባሕርይና በታሪክ ውስጥ ያከናወናቸውን ተግባራት ይገልጻል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ስላደረገልን መልካም ነገሮች–ስለ ሰጠን ደኅንነት፥ ስለ ጤንነታችን በረከት፥ ስለ ጥበቃው፥ ጉድለቶቻችንን ስለ መሙላቱ፥ ወዘተ... ይናገራል። ግን እግዚአብሔር ይህንን ሁሉ ያደረገልን ለምንድን ነው? የፍቅሩ ጠቀሜታዎች ተቀባዮች እንሆን ዘንድ ብቻ የተገለጸ ነው? አይደለም! መጽሐፍ ቅዱስ ያገኘናቸው በረከቶች ሁሉ ከእግዚአብሔር እንደተሰጡን የሚናገረው እግዚአብሔር ይመሰገንና ይከብር ዘንድ ነው። በኤፌሶን ውስጥ ያገኘናቸው በረከቶች ሁሉ ለኢየሱስ ክርስቶስ

ክብር እንደተደረጉ ተገልጾአል (ኤፌ. 1፡6፥ 12፥ 14፤ ኢሳ. 43፡7)። በዛሬ ጥናታችን እግዚአብሔር ለመረጠው ሕዝብ በሚሠራበት ጊዜ እንዴት ከፍተኛ ክብርና ምስጋና እንደሚቀበል እንመለከታለን። ሕዝቡ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ የምስጋናን መዝሙር በሚዘምርበት ጊዜ እግዚአብሔር ይባረካል። ነገር ግን የበለጠ የሚባርከው ሕዝቡ ለእርሱ እየተገዙ፥ ስለ ታላቁ አምላካቸው ለሌሎች እየተናገሩና እግዚአብሔር እነርሱን የመረጠበትን ምክንያት እየፈጸሙ ሲኖሩ ነው። ቃላችን በኑሮአችን ሲገለጽ እግዚአብሔር ይባረካል።

2ኛ ጥያቄ፡– ኢሳይያስ 43 አንብብ። ሀ) የዚህ ምዕራፍ ተደራሲ ማን ነው? ለ) በቁጥር 1 የእግዚአብሔርና የእስራኤል ግንኙነት የተገለጸው እንዴት ነው? ይህ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ካለው ግንኙነት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ሐ) ከቁጥር 1–6 እግዚአብሔር ለሕዝበ–እስራኤል እንዳደረገ ወይም እንደሚያደርግ የተናገራቸውን ነገሮች ዘርዝር። ይህ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የተፈጸመው እንዴት ነው? መ) ጣዖታትን የሚያመልኩ ሰዎች ከቁጥር 8–9 የተገለጹት እንዴት ነው? ሠ) እስራኤላውያን ምስክርነት የተጠሩት ለምንድን ነው? (ቁ. 10)። እግዚአብሔር በዚህ ክፍል ከአሕዛብ ጋር የተነጻጸረው እንዴት ነው? (ቁ. 8–13)። ረ) ከቁጥር 14–21 ለእስራኤላውያን የተሰጡት የተስፋ ቃሎች ምንድን ናቸው? እነዚህ በእስራኤል ታሪክ ውስጥ የተፈጸሙት እንዴት ነው? ሰ) ከቁጥር 22–28 እስራኤል ባለማድረጓ የተወቀሰችበት ነገር ምንድን ነው? ይህ ለአገራቸውና ለሕዝባቸው የሚያስከትለው ውጤት ምንድን ነው? ይህ ትንቢት የተፈጸመው መቼ ነበር?

1. እግዚአብሔር ሕዝቡን ከተበተኑባቸው አገሮች በመሰብሰብ ወደ አገራቸው ይመልሳቸዋል (ኢሳ. 43፡1–7)

ክርስቲያኑን ከሚፈታተኑት ዐበይት ጠላቶች አንዱ ፍርሃት ነው። ይህም የሞት፥ የስደት፥ የመገለል፥ ወዘተ... ፍርሃት ሊሆን ይችላል። በአንድ ሰው ልብ ውስጥ ፍርሃት በሚኖርበት ጊዜ በሕይወት እጅግ አስፈላጊ የሆኑትን ነገሮች ትቶ ለጊዜው ከፍርሃቱ የሚያላቅቀውን ነገር ይመርጣል። አይሁዶች የባቢሎን ሠራዊት ከተማቸውን ሲቆጣጠሩ አይተው በፍርሃት ተዋጡ። ይኸው ፍርሃት ምርኮኞች ሆነው ወደ ባቢሎን ሲሄዱና በሚሶጳጣሚያ ሸለቆዎች በሚገኙ ብዙ አገሮች ውስጥ ሲበተኑ እየናረ ይሄድ ጀመር። ብዙ አይሁዶች እግዚአብሔርን የማያውቁትን ጌቶቻቸውን በመፍራት የአባቶቻቸውን አምላክ ተዉ። እግዚአብሔር ይህንን የማጽናኛ መልእክት ለኢሳይያስ የሰጠው አይሁዶች ፍርሃታቸውን አሸንፈው በዘላለማዊ አምላክ ላይ ያላቸውን እምነት እንዲያጸኑ ለማድረግ ነበር። («አትፍራ» የሚለው ቃል ምን ያህል ተደጋግሞ እንደተጠቀሰ አጢን።) እግዚአብሔር አይሁዶች ሁለት

ዐበይት ነገሮችን በማወቅ ፍርሃታቸውን እንዲያስወግዱ አበረታቶአቸዋል። በመጀመሪያ፥ ከእርሱ ጋር ልዩ ግንኙነት ነበራቸው። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር በአገርና በግለሰብ ደረጃ ምን እንደሚያደርግላቸው ገልጾላቸዋል።

ሀ. የእግዚአብሔርና የሕዝቡ ግንኙነት (ኢሳ. 43፡1)

1. እግዚአብሔር እስራኤልን ፈጥሮአታል፤ ሠርቶአታልም። «መፍጠር» የሚለው ቃል ሁልጊዜም የእግዚአብሔርን የመጠንሰስ፥ የመቆጣጠርና የማቆየት ሉዓላዊ ተግባር ያመለክታል። አካላዊውን ዓለም ፈጥሮ እንዳኖረ ሁሉ፥ ሕዝበ-እስራኤልንም የፈጠረውና የሚያኖረው እግዚአብሔር ነው። «ሠራ» የሚለው አንድ ሸክላ ሠሪ ሸክላውን መርጦ በጥንቃቄ በመቅረጽ ለሰው ልጆች ደስታን የሚፈጥር ነገር የሚሠራበትን ሁኔታ የሚያመለክት ቃል ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር እስራኤልን በጥንቃቄ በመምረጥ ለእርሱ ክብርን የምታመጣ አገር አድርጎ ሠርቶአታል።

መጽሐፍ ቅዱስ የእስራኤልና የእግዚአብሔር ግንኙነት እንዴት እንደ ተጀመረ በግልጽ ይናገራል። እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለመመሥረት አልመረጠችም። ከአሕዛብ መካከል አብርሃምን መርጦ በማውጣት በእርሱ አማካኝነት እስራኤልን የፈጠረው እግዚአብሔር ነበር። ልዩ የቃል ኪዳን ግንኙነት የሚያደርግባትን አገር ለመፍጠር የወሰነው እግዚአብሔር ነበር። ለሚከተሉት አያሌ ምክንያቶች ሲባል እስራኤል ይህንን መገንዘብ ነበረባት።

<u>በመጀመሪያ፥</u> የእግዚአብሔር ሕዝብ መሆናቸው እግዚአብሔርን በመምረጥ ለመቀጠል ወይም ለእግዚአብሔር ለመታዘዝ በመቻላቸው ላይ እንዳልተመሠረተ ማወቅ ነበረባቸው። እግዚአብሔር የመረጣቸው እነርሱ እርሱን ከመምረጣቸው ከረዥም ዓመታት በፊት ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት በእነርሱ ተግባር ላይ የተመሠረተ አልነበረም።

ይህ እውነት ሁለት ስሜቶችን ሊያስከትል ይገባ ነበር። 1) በዓለም እየሆነ ካለው ነገር ባሻገር ለእግዚአብሔር ልዩ መሆናቸውን በማመልከት የደኅንነትን ዋስትና ያጎናጽፋቸዋል። እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ያለው ግንኙነት በምድረ ይሁዳ በመኖራቸው፥ ንጉሥና ቤተ መቅደስ ያላቸው ሰዎች በመሆናቸው፥ ብዙ ሕዝብ በመሆናቸው፥ ወዘተ... ላይ አይደገፍም ነበር። ይህ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫና ጸጋ ላይ የተመሠረተ ነበር። እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲሆኑ መርጧቸዋል። ይህንንም ምርጫ ማንም ሊለውጠው አይችልም። 2) ትሑታን ሊያደርጋቸው ይገባ ነበር። እግዚአብሔር የመረጣቸው

ከሌሎች አገሮች የተሻሉ ወይም የበዙ በመሆናቸው አልነበረም። በእነርሱ በኩል ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ለመጀመር ምክንያት የሆነ ምንም ነገር አልነበረም። ይህ ሙሉ ለሙሉ የእግዚአብሔር ሉዓላዊ ተግባር ነበር። ስለሆነም ከሌሎች አገሮች የተሻሉ እንደሆኑ በማሰብ ሊመኩ አይችሉም ነበር። የሚታበዩበት ምክንያት አልነበራቸውም።

ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ ሉዓላዊ መብቶች እንዳሉት መገንዘብ ነበረባቸው። እንደ ሕዝብና አገር የፈጠራቸው እርሱ በመሆኑ፥ እነርሱን የመሸለምም ሆነ የመቅጣት መብት ነበረው። እነርሱ ግን እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ከእነርሱ ጋር እንዴት እንደሠራ የመጠየቅ መብት አልነበራቸውም። አንድ ብዕር የገዛ ሰው ብዕሩን ከመወርወር አንሥቶ እንደፈለገ የመጠቀም መብት እንዳለው ሁሉ፥ እግዚአብሔርም በሕዝቡና በእነርሱ ላይ እንዲፈጸም በሚፈቅደው ነገር ላይ ሙሉ መብት አለው። ወደ ምርኮ በመስደድ ሊቀጣቸው መብት ነበረው። የተሻለ ነው ብሎ በሚያስብበት ጊዜ ደግሞ ከምርኮ የመመለስ መብት ነበረው።

በዚህ ምንባብ ትኩረት የተሰጠው ግን የመረጣቸው እግዚአብሔር እንደመሆኑ በእርሱ ተማምነው ሊኖሩ እንደሚችሉ ከማሳየቱ ላይ ነው። እርሱ ይጠነቀቅላቸዋል። እግዚአብሔር የእርሱ የሆነውን ነገር ይንከባከባል እንጂ አንሥቶ አይወረውርም።

አዲስ ኪዳን እንደሚያስተምረው፥ እኛም ብንሆን መጀመሪያ ኢየሱስ ክርስቶስን አልመረጥነውም። እግዚአብሔር ግን መረጠን (ዮሐ. 15፡16 አንብብ)። መቼም ቢሆን እኛ ልዩ ሰዎች በመሆናችን፥ ለእግዚአብሔር አንድ ጥሩ ነገር ስላደረግን፥ ወይም እግዚአብሔርን ስለመረጥን፥ እግዚአብሔር እኛን ልጆቹ ለማድረግ እንደተገደደ አድርገን ማሰብ የለብንም። ደኅንነት ሁልጊዜም በነፃ የሚገኝ ስጦታ እንጂ ሠርተን የምናጠራቅመው ሀብት አይደለም (ኤፌ. 2፡8–9)። እግዚአብሔር ሁላችንንም የሚጠራንና ወደ ልባችን ገብቶ ልጆቹ የሚያደርገን በጸጋው ነው። እንዲሁም ደግሞ እኛ የእግዚአብሔር ነን። እንዲያውም በእኛ ላይ ሁለት የባለቤትነት መብቶች አሉት። መጀመሪያ በመፍጠር መብቱ የእርሱ ነን። ሁለተኛ በኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት የእርሱ ስላደረገን የባለቤትነት መብት አለው (1ኛ ቆሮ. 6፡20፤ 7፡23)።

3ኛ ጥያቄ፡– እግዚአብሔር እንደ ፈጠረንና እንደ ሠራን መገንዘቡ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ጋር ያለንን ግንኙነት እንዴት ሊለውጠው ይገባል?

2. እግዚአብሔር እስራኤልን ተቤዠቶአታል። ሰው ባሪያን ገዝቶ ነፃ እንደሚያወጣ ወይም በባርነት የተገዛ ሰው አርነት ይወጣ ዘንድ ዘመዱ ገንዘብ እንደሚከፍልለት፥ እግዚአብሔር እስራኤልን ገዝቶአታል። ይህንንም ያደረገው አይሁዶችን ለኃጢአት፥ ለዓለምና ለአሕዛብ በባርነት ከመገዛት በመታደግ ነው። እግዚአብሔር አይሁዶችን ለባቢሎን ከመገዛት ያድናቸዋል።

3. እግዚአብሔር አይሁዶችን በስማቸው ጠርቶአቸዋል። አንድን ሰው በስሙ መጥራት ከዚያ ሰው ጋር የግል ግንኙነት እንዳለህ ያሳያል። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ እግዚአብሔርም አይሁዶችን በግል ያውቃቸው ነበር። አይሁዶች የቤተሰቡ አካላት እንጂ እንግዶች አልነበሩም። ይወዳቸው ነበር። የእያንዳንዳቸውን ስም ከማወቁም በላይ ለእያንዳንዳቸው ዕቅድ ነበረው። እኛም እንደዚሁ የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል በመሆናችን እግዚአብሔር ስም ሰጥቶናል (ራእ. 2፡17፤ 3፡12፤ 22፡4)።

4. አንተ የእኔ ነህ። ኢሳይያስ አይሁዶች የእግዚአብሔር ንብረት በመሆናቸው ላይ አጽንኦት ሰጥቶአል። ከእግዚአብሔር ጋር የተለየ ግንኙነት ነበራቸው። ምንም እንኳ ባሪያ ሊያደርጓቸው ቢችሉም የባቢሎናውያን ንብረት አልነበሩም። እነርሱ የእግዚአብሔር ነበሩ። ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እኛ እንደተናገረው፥ በእጆቹ ስለያዘን ማንም ሊነጥቀን አይችልም (ዮሐ. 10፡28–29)።

4ኛ ጥያቄ፡– ሀ) አይሁዶች ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነቶች የሚያብራሩት እነዚህ ነገሮች እያንዳንዳቸው ለክርስቲያኖችም እውነት የሚሆኑት እንዴት ነው? ለ) ለክርስቲያኖች እነዚህን እውነቶች ማወቁ አስፈላጊ የሚሆነው ለምንድን ነው?

ለ. እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር ካለው ግንኙነት ሳቢያ በሕዝቡ ፈንታ ይሠራል (ኢሳ. 43፡2–7)

እግዚአብሔር ለሰዎች የሚያደርገው ነገር ከእርሱ ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ የተመሠረተ ነው። እግዚአብሔር የአማኞችም የማያምኑት ሰዎችም አምላክ ስለሆነ በስጦታዎቹ ያንበሸበሻቸዋል። መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለዳኑትም ላልዳኑትም ዝናብን እንደሚሰጥ ይናገራል (ማቴ. 5፡45)። ነገር ግን የእግዚአብሔር ልዩ ስጦታዎች ልጆቹ ለሆኑትና ከእርሱ ጋር ልዩና ግላዊ ግንኙነት ለሚያደርጉት ብቻ የተጠበቀ ነው። እግዚአብሔር ለጉድለታቸው በመቆርቆር ጉድለታቸውን ያሟላላቸዋል። ለዚህም ነው አንድ ክርስቲያን ክርስቲያን ካልሆነው ሰው በላቀ ልበ ሙሉነት ሊጸልይ

የሚችለው። እግዚአብሔር ከሚጸልየው ሰው ጋር ባለው ግንኙነት ላይ በመመሥረት ምላሹን ይሰጣል።

እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር ልዩ ግንኙነት ስለነበረው አንዳንድ ነገሮችን እንደሚያደርግላቸው ቃል ገብቶአል።

1. ወደ ምርኮ በሚሄዱበት ጊዜም ሆነ እዚያ በሚኖሩባቸው ጊዜያት እግዚአብሔር ሕዝቡን ይጠብቃል። እንዲሁም ልጆቹን ከሚጎዳቸው ከማንኛውም ነገር በመጠበቅ ወደ ይሁዳ እንዲመለሱ ያደርጋል። ኢሳይያስ ለአይሁዶች ከሚደረጉት እንክብካቤዎች ሁለቱን በምሳሌነት ጠቅሶአል።

በመጀመሪያ፥ የውኃ ችግር ነበር። እግዚአብሔር ወደ አገራቸው ለመመለስ ከፍተኛ መሰናክል ከሚፈጥሩት ወንዞች እንደሚጠብቃቸው ቃል ገብቶአል። በረሾሙ ጉዞአቸው በደህና መመለስ እንዲችሉ በርካታ ወንዞችን ማቋረጥ ነበረባቸው። እግዚአብሔር አስፈላጊ ከሆነ ተአምራትን በማድረግ ጭምር ከባቢሎን ወደ እስራኤል በሚወስደው ረሾም መንገድ ላይ ጥበቃውን እንደሚያበዛላቸው ገልጾአል። ኢሳይያስ እስራኤላውያን ከግብፅ በወጡ ጊዜ እግዚአብሔር እንዴት ቀይ ባሕርን (ዘጸ. 14፡21–22) እና የዮርዳኖስን ወንዝ (ኢያ. 3፡14–17) እንዳሻገራቸው እያሰበ ነበር። ኢሳይያስ የአደገኛ ወንዞችን ምሳሌዎች የተጠቀመው ሕዝቡ ወደ ከነዓንም ሆነ ወደ መንግሥተ ሰማይ በሚያደርጉት መንፈሳዊ ጉዞ እግዚአብሔር እንዴት እንደሚጠብቃቸው ለማሳየት ሳይሆን አይቀርም።

<u>ሁለተኛ</u>፥ እግዚአብሔር ከእሳት እንደሚጠብቃቸው ተናግሮአል። ይህ እሳት ምንን ያመለክታል? ይህ የምናውቀው ዓይነት እሳት ይሆን? አጠራጣሪ ነው። ኢሳይያስ ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ቢኖር እስራኤላውያን ወደ ይሁዳ በሚመለሱበት ጊዜ ስለሚያጋጥሟቸው ስደቶች፥ ወንበዴዎችና ክፉ ጠላቶች ይመስላል። ይህም ሆኖ፥ እግዚአብሔር ሲድራቅ፥ ሚሳቅንና አብድናጎን ከእሳት እንዳዳናቸው እናውቃለን (ዳን. 3፡25–27)። ምንም እንኳ በእሳት እቶን ውስጥ ቢጣሉም እግዚአብሔር ከእሳት አደጋ ታድጎአቸዋል። እነዚህ ሦስት ሰዎች ከአንድ መቶ ዓመታት በፊት የተጻፈውን ይህንኑ የትንቢተ ኢሳይያስን መልእክት አንብበው ይሆን ብርታትን የተላበሱት?

ውኃውም ሆነ እሳቱ እግዚአብሔር የሚያጋጥማቸውን ፈተና ሁሉ እንዴት እንደሚያሻግራቸው የሚያመለክቱ ተምሳሌታዊ አገላለጾች ናቸው። ኢሳይያስ የሚጽፈው ወደ ምርኮ ስለመሄዳቸው ከሆነ፥ መለኮታዊ ፍርድ ተቀብለው በጠላቶቻቸው በሚገዙበት ጊዜ እንኳ እግዚአብሔር በፍጹም እንደማይተዋቸው ወይም እንደማይጥላቸው

እየገለጸ ነበር ማለት ነው። ምን ያህል መከራ ሊቀበሉ እንደሚገባ በመወሰን በዚያው በምርኮአቸው ውስጥ ይጠብቃቸዋል።

2. እግዚአብሔር ሕዝቡን ከባቢሎን ይቤዣል። እግዚአብሔር ለዚህ የተስፋ ቃል አጽንኦት ለመስጠት ስለ ማንነቱ አስታውሶአቸዋል። እርሱ ከሕዝቡ ጋር ልዩ ግንኙነት የሚያደርግ፥ «የእስራኤል ቅዱስ» የሆነ ኃያል አምላክ ነው። እርሱ ለጉድለቶቻቸው ሁሉ መፍትሔ የሚሰጥ አዳኛቸው ነበር። ይህም ያድናቸው ዘንድ እግዚአብሔርን ስለመረጡት ሳይሆን እርሱ ስለመረጣቸው ነው። እግዚአብሔር አይሁዶችን ከባርነት ገዝቶ ነፃ እንደሚያወጣቸው (እንደሚቤዣቸው) ተናግሮአል። ነገር ግን እግዚአብሔር የሚከፍለው ለማን እና ምን ነበር? በዚህ ስፍራ ባይገለጽም፥ ቤዛ የሚከፈለው ለቂሮስና ለሜዶ-ፋርስ ሠራዊት ነበር። ባቢሎናውያንን በውጊያ አሸንፈው በባቢሎን የተያዙትን ሰዎችና መሬቶች የሚወስዱት ሜዶ-ፋርሳውያን ነበሩ። ሜዶ-ፋርሳውያን አይሁዳውያን ወደ አገራቸው ይሄዱ ዘንድ ይለቁአቸዋል። እግዚአብሔር የሚሰጣቸው ምን ነበር? እግዚአብሔር አንዳንድ ኃያላን አገሮችን እንደ ግዛታቸው አካል አድርጎ እንደሚሰጣቸው ገልጾአል። የቂሮስ ግዛት ምን ያህል እንደሚሰፋ ለማሳየት፥ እግዚአብሔር ኢትዮጵያን፥ ግብፅንና ሳባን ጠቅሶአል። እነዚህም ከይሁዳ በስተ ደቡብ የሚገኙ ሦስት ኃያላን አገሮች ነበሩ። ኢትዮጵያና ሳባ ከጥንት ጀምሮ የጠበቀ ግንኙነት ነበራቸው።

እግዚአብሔር ይህንን የሚያደርገው ለምን ነበር? አይሁዶች በምድር ላይ ከሚገኙት ሌሎች ሕዝቦች ሁሉ የተሻሉ በመሆናቸው ነበር? ከሌሎች በላይ ጻድቃን ስለነበሩና ልዩ እንከብካቤ ስለሚገባቸው ነው? አይደለም! ይህንን የሚያደርገው ከአይሁዶች ጋር ልዩ ግንኙነት ስለነበረው ነው! በእግዚአብሔር ዓይኖች ፊት የከበሩና የተወደዱ ነበሩ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍቅር ውሳኔ እንጂ ስሜት አይደለም። እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር ግንኙነት ለማድረግ የወሰነ በመሆኑ፥ ለእነርሱ የሚሻላቸውን በመፈጸም ጉድለታቸውን ለመሙላት ቆርጦአል። ይህም የግንኙነቱ አካል ነበር።

3. እግዚአብሔር አይሁዶችን ከተበተኑባቸው አገሮች ሁሉ፥ ከምሥራቅ፥ ከምዕራብ፥ ከደቡብና ከሰሜን ለመሰብሰብ ቃል ገብቶአል። ከዓለም ሁሉ ወደ አገራቸው ይመልሳቸዋል። ይህ የእግዚአብሔር የተስፋ ቃል በታሪክ ሁሉ በተለያዩ መንገዶች ሲፈጸም ቆይቷል። በባቢሎን ግዛቶች የነበሩ አይሁዶች ወደ ይሁዳ እንዲመለሱና በዚያ እንዲኖሩ በተደረገበት በዘሩባቤል፥ በዕዝራና በነህምያ ዘመን በቀዳሚነት ተፈጽሞአል። ብዙ ሰዎች በተለያዩ የዓለም ክፍሎች የሚኖሩ አይሁዶች ወደ አ ገራቸው ተመልሰው መንግሥት

በመሠረቱበት በ1948 ዓ.ም. እንደገና እንደተፈጸመ ያስባሉ። ብዙ የቅድመ-ሺህ - ዓመታት አመለካከት አራማጆች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ለመግዛት በሚመጣበት ጊዜ አይሁዶች በከፍተኛ ደረጃ ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚሰበሰቡ ያምናሉ። ዛሬ በፍልስጥኤም አገር ከሚኖሩት አይሁዶች በውጭ አገር የሚኖሩት በቁጥር ይልቃሉ። በዚያን ጊዜ ይህ ጥቅስ ሙሉ ተፈጻሚነት ይኖረዋል። የአልቦ-ሺህ-ዓመታትና የድኅረ-ሺህ-ዓመታት አመለካከት አራማጆች ይህንን ምንባብ ከደኅንነት ርቀው የጠፉት ኃጢአተኞች ወደ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሚመለሱና አንድ ቀን ሕዝበ-እግዚአብሔር ሁሉ በእግዚአብሔር ዙፋን ፊት ተሰብስበው እንደሚያመልኩት የሚያሳይ ነው ብለው ይተረጉሙታል።

ኢሳይያስ በተጨማሪም እግዚአብሔር ማንን ወደ ይሁዳ እንደሚመልስ ገልጾአል። የመጀመሪያ አይሁዳዊ የሆነውን አብርሃምን እንደጠራው ሁሉ በስማቸው የጠራቸውን አማኝ አይሁዳውያን እንጂ የማያምኑትን እንዳልሆነ «በስሜ የተጠራውን» በማለት አስረድቷል። ምንም እንኳ ይህ የትኛውንም አይሁዳዊ ሊያመለክት ቢችልም፥ እግዚአብሔር በዚህ ስፍራ ለማሳየት የፈለገው ወደ ይሁዳ የሚመለሱት ከእርሱ ጋር ልዩ ግንኙነት ያላቸውና ሊያከብሩት የሚፈልጉት አይሁዶች መሆናቸውን ነው። ምናልባትም ኢሳይያስ በአሕዛብ ምድር ለሚኖሩት አይሁዶች እውነተኛ የእግዚአብሔር ልጆች ከሆኑ የሚኖሩባቸውን አገሮች ለቅቀው ወደ ይሁዳ እንደሚመለሱ ለመናገር እየሞከረ ይሆናል። የሚያሳዝነው ግን ከሰባ ዓመታት ምርኮ በኋላ ብዙ አይሁዶች ከነበሩባቸው አካባቢዎች ጋር በመስማማታቸው ወደ ይሁዳ ለመመለስ አለመፈለጋቸው ነው። እግዚአብሔር በመረጠላቸው ምድር ከመኖር ይልቅ የአሕዛብን ምድር ምቹ ኑሮ መረጡ። ይህንንም በማድረጋቸው ከእግዚአብሔር መንፈሳዊ በረከት ይልቅ ሥጋዊ ምቾትን እንደመረጡ አመልክተዋል።

ጳውሎስ ሦስት ዓይነት አይሁዶች እንዳሉ ገልጾአል። እነዚህም ከየትኛውም ዘር ተወልደው እንደ አብርሃም በእግዚአብሔር የሚያምኑ፥ ከአይሁድ ዘር ሆነው እንደ አብርሃም በእግዚአብሔር የሚያምኑና ከእግዚአብሔር ጋር ሕያው ግንኙነት ሳይኖራቸው በዘር ትውልድ ብቻ አይሁዳዊ የሆኑ ናቸው (ሮሜ 2፡25-29፤ 9፡6-13፤ ገላ. 3፡6-9፥ 28-29፤ 4፡21-31)። በተመሳሳይ ሁኔታ፥ ራሳቸውን ክርስቲያኖች አድርገው የሚቆጥሩ ሁሉ ክርስቲያኖች አይደሉም። ምክንያቱም ክርስትና የውልደት ውጤት ሳይሆን አንድ ሰው ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ነው። ለዚህ ነው ክርስቲያን ወላጆች ልጆቻቸው

በቤተሰባዊ እምነት ላይ ከመደገፍ ይልቅ ክርስቶስን ለመከተል የግል ውሳኔ ያደርጉ ዘንድ ወንጌሉን በግልጽ ማብራራት የሚኖርባቸው።

5ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ምን ያህል ሰዎች ክርስቲያን ወላጆች ስላሏቸው ወይም ወደ አንድ ቤተ ክርስቲያን በመሄዳቸው ምክንያት ክርስቲያኖች እንደሆኑ እንደሚያምኑ ግለጽ። ለ) እነዚህ ሰዎች አንድ ሰው የእግዚአብሔር ልጅ ስለሚሆንበት መንገድ ያላቸው የተሳሳተ አሳብ ምንድን ነው? ሐ) በቤተክርስቲያን ውስጥ የሚገኙ ልጆች ወንጌሉን እንደሚያውቁና ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል በግል ደረጃ መወሰናቸውን ለመረዳት ቤተ ክርስቲያንህ ምን እያደረገች ነው? መ) ይህ ይበልጥ ፍሬያማ ውጤት ይኖረው ዘንድ ምን አሳብ ታቀርባለህ?

ኢሳይያስ እግዚአብሔር ሰዎችን ለምን ለራሱ እንደሚጠራ አመልክቷል። ይህ በቀዳሚነት ለእኛ ጥቅም ሳይሆን ለእግዚአብሔር ክብር ነው። አምልኮአችንንና ስለ ደኅንነታችን የምንሰጠውን ገለጻ ዘወር ብለን ካየን ብዙውን ጊዜ እግዚአብሔር ባደረገልን ነገር ላይ የተመሠረተ ነው። ይህም በሰው ላይ ያተኮረ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ብዙውን ጊዜ ደኅንነትን የሚገልጸው ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር ነው። የእግዚአብሔር ሥራ በቀዳሚነት ለእግዚአብሔር ጥቅም ነው። በዚህ ስፍራ ሕዝቡ የሚሰበሰበው ለእግዚአብሔር ክብር እንደሆነ ተገልጾአል። ምሑራን «መፈጠር» እና «መሠራት» የሚሉት ቃላት በዘፍጥረት አንድ የቀረበውን የመጀመሪያውን የፍጥረት ታሪክ እንደሚያስረዱ ይናገራሉ። እግዚአብሔር የመጀመሪያውን ዓለም ለራሱ ክብር እንደፈጠረ ሁሉ አሁንም ሰዎች ከእርሱ ጋር ዘላለማዊ ቃል ኪዳን እንዲያደርጉ በመጥራት ዓለምን ዳግም ለክብሩ ይፈጥራል።

2. እግዚአብሔር የራሱን ኃያልነትና የጣዖት አምላኪዎችን ኃይል–አልባነት ያሳያል (ኢሳ. 43፡8–13 አንብብ)።

ኢሳይያስ ቀደም ሲል ወደተገለጸው የፍርድ ችሎት ምስል በመመለስ በአንድ ወገን በእግዚአብሔርና በሕዝቡ፥ በሌላ ወገን ደግሞ በእግዚአብሔር በማያምኑት አሕዛብና በጣዖቶቻቸው መካከል የሚካሄደውን ተግዳሮት ያቀርባል። ሉዓላዊ ንጉሥና የመጨረሻ ዳኛ የሆነው እግዚአብሔር ሁለት ዓይነት ሰዎች ከፊቱ ቀርበው የበለጠ ኃይል በመያዙ ምክንያት ሊመለክ የሚገባው ማን እንደሆነ እንዲያረጋግጡ አዘዘ። <u>መጀመሪያ</u>፥ እግዚአብሔር ዓይኖች እያሏቸው የማያዩትንና ጆሮዎች እያሏቸው የማይሰሙትን ጠራ። የእግዚአብሔር ሕዝብ የሆኑት አይሁዶች መንፈሳዊ ዕውራንና ደንቆሮዎች እንደሆኑ ከትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ በተደጋጋሚ አይተናል። የእግዚአብሔርን ቃል ሰምተው ሊከተሉት የሚገባቸው እነርሱ ሆነው ሳለ ይህንኑ አላደረጉም። ስለሆነም በዚህ ክፍል እግዚአብሔር ያላመኑትንና ንስሐ

ያልገቡትን አይሁድ ለፍርድ በፊቱ እንዲቀርቡ ያዝዛል። ሁለተኛ፥ እግዚአብሔር ወደ እርሱ ላለመምጣት የማያቋርጥ ዓመፅ የሚያካሂዱትን የማያምኑ የዓለም ሕዝቦች ያዝዛል። እነዚህ ሁለት ቡድኖች ከፍርድ ችሎቱ አንድ ወገን ይሰበሰባሉ። በሌላኛው የፍርድ ችሎት ወገን እግዚአብሔርና በታማኝነት ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖሩ ጥቂት አይሁዶች ይቀርባሉ። እነዚህም አምልኮተ ጣዖትን እምቢ ብለው በሕይወታቸው እግዚአብሔርን ያስከበሩ ሰዎች ናቸው።

«ማን ነው ታላቅ?» የሚለው ሙግት እስራኤል በባቢሎን እንደምትማረክና ከዚያ ተለቅቃ ወደ ተስፋዪቱ ምድር እንደምትመለስ ለመተንበይ በመቻል ላይ ያተኮረ ነበር። ይህንን ያደረገው እግዚአብሔር ነቢር ወይስ የአሕዛብ አማልክት? በዚህ ጊዜ ሁለት ዓይነት የምስክርነት ቡድኖች ተጠሩ። እግዚአብሔር የአሕዛብ ጣዖታት አይሁዳውያንም ሆኑ አሕዛባውያን በሆኑት ተከታዮቻቸው ትንቢት መናገር አለመናገራቸውን እንዲያስመሰክሩ ጠየቀ። እነዚህ አማልክት ስለ ወደፊት የተናገሩት ትንቢት ባለመኖሩ የምስክርነት ቃሉን የሚሰጥ ሰው አልነበረም። ከዚያም እግዚአብሔር የመጽሐፉን ሕዝብ ማለትም እስራኤላውያንን ጠራ። እስራኤላውያን እግዚአብሔር በኢሳይያስ በኩል ከምርኮ እንደሚለቀቁ የተነበየ መሆኑን ያውቁ ነበር።

ስለሆነም እግዚአብሔር ከጣዖታት እንደሚበልጥና አምልኮና ምስጋና የሚገባው ብቸኛ አምላክ ራሱ መሆኑን አረጋገጠ። ከመፈጸሙ ከረኹም ዓመታት በፊት እግዚአብሔር ሕዝቡ ከምርኮ ወደሚመለስበት አቅጣጫ ስለሚመሩት ክስተቶች ትንቢት ተናግሯል። ኢሳይያስ ሕዝቡ ከባቢሎን የሚለቀቅበት ጊዜ እንደ ቀረበ አስመስሎ እንደ ጻፈ አትዘንጋ። በኋላ እነዚህ ዓመታት እየገፉ ሲሄዱ እግዚአብሔር ቀደም ሲል ከ150 ዓመታት በፊት ነፃ እንደሚወጡ በኢሳይያስ በኩል እንደተናገረ ገለጸላቸው። ይህም እግዚአብሔር ከአሕዛብ በላይ ልቆ የሚገኝ አምላክ መሆኑን ያመለክታል። ስለሆነም ሕዝቡ እግዚአብሔርን ብቻ ለማምለክ መጠንቀቅ ነበረባቸው። እግዚአብሔር የወደፊትን መናገር ብቻ ሳይሆን ታሪክንም የሚቆጣጠር አምላክ ነው።

አይሁዶች የአጽናፈ ዓለሙ ሉዓላዊ አምላክ በሆነው ብቸኛ አምላክ ማመን ነበረባቸው። ይህ «ማመን» የሚለው ቃል አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ብቻ አምላክ እንደሆነ የማወቅን ምሑራዊ አቅጣጫ ያሳያል። እግዚአብሔርን የሚገደው ግን ትክክለኛው እውቀት ብቻ ሳይሆን ያወቁትን መኖሩ ጭምር ነው። እግዚአብሔር ብቻውን እውነተኛ አምላክ ከሆነ፥ አይሁዶች ሌሎችን ጣዖታት ማምለክም ሆነ መፍራት አይኖርባቸውም ነበር። ስለሆነም የትኛውም ሌላ ዓይነት አምልኮ ተቀባይነት የለውም። እግዚአብሔር ብቸኛ አዳኝ ስለሆነ

ሰዎችንም ሆነ ጣዖታት ተብዬ ነገሮችን መከተሉ አስፈላጊ አልነበረም። እግዚአብሔር እንደ ሉዓላዊና እውነተኛ አምላክ ሕዝቡን እንደሚጠብቃቸው ቃል ገብቶላቸዋል። ሕዝቡን ከእግዚአብሔር እጆች የሚነጥቅ ምንም ዓይነት ሰማያዊ ወይም ምድራዊ ኃይል አልነበረም። ወደ ሕይወታቸው የሚመጣውን ነገር ሁሉ የሚቆጣጠረው እግዚአብሔር ነበር። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ በመሆኑ ለመሥራት ሲነሣ የሚከለከለው አልነበረም።

6ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ክርስቲያኖች እግዚአብሔር ሉዓላዊና አዳኝ እንደሆነ ይናገራሉ። ነገር ግን ክርስቲያኖች የሚፈሯቸውና በእግዚአብሔር እንደማይተማመኑ የሚያሳዩ አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው? ለ) በእግዚአብሔር አምናለሁ ማለቱ ያንኑ እውነት በዕለት ተዕለት ሕይወት ከመግለጥ የሚቀልለው ለምንድን ነው?

3. እግዚአብሔር በዳግማዊ ዘጸአት እስራኤልን ይቤዣል (ኢሳ. 43፡14–21 አንብብ)

ለክርስቲያኖች በታሪክ ከሁሉም የሚልቀው ክስተት የኢየሱስ ክርስቶስ የመስቀል ላይ ሞት ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በኃጢአታችን ምክንያት የተፈረደብንን ቅጣት ለመክፈል በመስቀል ላይ ሞቶልናል። ለብሉይ ኪዳን አይሁዶች ግን ከሁሉም የሚበልጠው ክስተት ከግብፅ መውጣታቸው ነው። አይሁዶችን ከባርነት አውጥቶ ወደ ተስፋዪቱ አገር የወሰዳቸው ይኸው ክስተት ነበር። መዝሙረ ዳዊትና የነቢያት መጻሕፍት ስለዚሁ ጉዳይ አጥብቀው የሚናገሩት ለዚህ ነው። በዚህ ምንባብ ግን እግዚአብሔር አይሁዶች ወደ ኋላ ማየታቸውን አቁመው ከባቢሎን ወደ ተስፋዪቱ ምድር በሚወስዳቸው የወደፊት ዘጸአት ላይ እንዲያተኩሩ ተነግሯቸዋል።

እግዚአብሔር ሕዝቡን ለሁለተኛ ጊዜ በመቤዠት ነፃ ያወጣቸዋል። እግዚአብሔር ለሕዝቡ በቤዛነት የሚከፍለው ዋጋ ምንድን ነው? ባቢሎናውያንን ወይም ከለዳውያንን ሊሆን ይችላል። (ከለዳውያን የሚለው የባቢሎናውያን ሌላው ስያሜ ነው።) ባቢሎናውያን የጤግሮስንና የኤፍራጥስን ወንዞች ተሻግረው ላይና ታች ይመላለሱ የነበረ ሲሆን፥ እስከ ፋርስ ባሕረ ሰላጤ ድረስ በመርከብ ይሄዱ ነበር። በአንድ ወቅት ወደ ባቢሎን ሸቀጣ ሸቀጦችን ለማምጣት ያገለግሉ የነበሩት መርከቦች በዚህ ጊዜ ከፋርስና ሜዶን ወታደሮች ለማምለጥ ያገለግላሉ። የተናገረው ነገር እንደሚፈጸም ለማረጋገጥ እግዚአብሔር ባሕርያቱን የሚገልጹትን የተለያዩ ስሞች ዘርዝሮአል። እነዚህም የሚቤዥ፥ የእስራኤል ቅዱስ፥ ቅዱሳችሁ፥ የእስራኤል ፈጣሪና ንጉሣችሁ ናቸው። እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ በመሆኑ እነዚህ የተስፋ ቃሎች ተፈጻሚነት ይኖራቸው ነበር።

እግዚአብሔር የተለያዩ ስሞችን በመዘርዘር ስለ ባሕርያቱ መግለጽ ብቻ ሳይሆን ቀደም ሲል ቀይ ባሕርን (እና የዮርዳኖስን ወንዝ) የከፈለበትንም ሁኔታ አስታውሶአቸዋል። የግብፅን ሠራዊት እስራኤላውያንን እንዲከተሉ በመጥራት ከባሕሩ ውስጥ ያሰመጣቸው እግዚአብሔር ነበር።

እግዚአብሔር የቀደመ ኃይሉን ከገለጸ በኋላ ያንን እንዲረሱት ነገራቸው። ሕዝቡ ባለፈው ታሪክ ሳይሆን በሁለተኛው ዘጸአት እግዚአብሔር በሚያከናውንላቸው ተግባር መኖር ይገባቸው ነበር። እግዚአብሔር በመጀመሪያው ዘጸአት ጊዜ ሕዝቡን እንደጠበቀው ሁሉ አሁንም ይህንኑ ያደርግ ነበር። በመጀመሪያው ጊዜ እንዳደረገው ውኃ ሲጠማቸው እያጠጣቸው በምድረ በዳ ይመራቸዋል (ዘጸ. 17፡6)። ከባቢሎን ካስወጣቸው ጊዜ አንሥቶ ወደ ተስፋዪቱ ምድር በሰላም እስከደረሱበት ጊዜ ድረስ የሚያስፈልጋቸውን ሁሉ ያሟላላቸዋል። አሁንም እነዚህ የጥበቃ ገለጻዎች እግዚአብሔር ወደፊት ለሕዝቡ የሚያመጣቸውን በረከቶችና ጥበቃዎች በተምሳሌትነት የሚያሳዩ ናቸው።

እግዚአብሔር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል በመስቀሉ ላይ ያደረገልንን ልንረሳ አይገባም። ያም ሆኖ ባለፈው ሳይሆን ለወደፊቱ መኖር ያሻናል። ለደኅንነታችን ዋጋ የከፈለና ወደ መንግሥተ ሰማይ በሚያስኬድ እምነት የሞላን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ዋናው ጥያቄ አሁን እንዴት እየኖርን ነው የሚል ይሆናል። እግዚአብሔር አሁን በሕይወታችን ምን እየሠራ ነው? እግዚአብሔር የአሁን አምላክ ነው። በሥራ ላይ ነውና ተግባሮቹን ልብ ልንል፥ ልናመልከውም ይገባል። ለእኛ የገባው ቃል አይለወጥም። የሚያስፈልገንን ሁሉ በየዕለቱ ይሰጠናል። ይህም ወደ መንግሥተ ሰማይ እስከንሄድ ይቀጥላል።

7ኛ ጥያቄ፡– መዝሙር 103 የእግዚአብሔርን ቸርነት እንዳንዘነጋ ያስታውሰናል። እግዚአብሔር ባለፈው ሳምንት ወይም ሳምንታት ያደረገልህን ነገሮች ዘርዝር። እግዚአብሔር ወደ ፊት እንደሚሰጥህ የተስፋ ቃል የገባባቸውን በረከቶች ዘርዝር። እግዚአብሔር ባለማቋረጥ ስለሚያደርግልህ ጥበቃና ችሮታ፥ ብሎም ወደፊት ስለሚጠብቁህ በረከቶች ታመሰግነው ዘንድ ጊዜ ውሰድ።

ክፍሉ እግዚአብሔር እስራኤላውያንን ለምን እንደመረጣቸው በማስገንዘብ ይቋጫል። የተመረጡት ከዓለም ሕዝቦች የተሻሉ ወይም የሚበዙ በመሆናቸው አልነበረም። እግዚአብሔር እንዲወዳቸው የሚያደርግ ምንም መልካም ነገር አልነበራቸውም። ነገር ግን እግዚአብሔር በነፃ ፈቃዱ መረጣቸው። አይሁዶች ሁልጊዜም እግዚአብሔር እንዲመርጣቸው የሚያደርግ ምንም ነገር እንደሌላቸው

ማስታወስ ነበረባቸው። ስለሆነም ያደረገላቸውንና ወደፊትም የሚያደርግላቸውን እያሰቡ ሊያመሰግኑት ይገባ ነበር። ለብዙ ጊዜ ክርስቲያኖች የነበረን ሰዎች ከምንፈጽማቸው አደገኛ ስሕተቶች አንዱ ሕይወታችን ሁሉ የእግዚአብሔር የጸጋውና የምሕረቱ ስጦታ እንደሆነ መዘንጋታችን ነው። ከእኛ ምንም ነገር አልጠየቀም። ይገባናል የምንለው ነገር ቢኖር ሞት ብቻ ነው። ነገር ግን በምስጋናና በአክብሮት እንኖርለት ዘንድ እግዚአብሔር ዛሬ በእጃችን ያለውን ነገር ሁሉ ሰጥቶናል።

8ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ያገኘናቸውን በረከቶች እግዚአብሔር በጸጋው እንደሰጠን ዘንግተን የመብት ጥያቄ የምናነሣው ለምንድን ነው? ለ) ሁልጊዜም በእግዚአብሔር ፊት የተዋረደ መንፈስ እንዳለንና ለሚሰጠን ነገር ሁሉ አመስጋኞች መሆናችንን ለማሳየት ልናደርጋቸው የሚገቡን አንዳንድ ነገሮች ምንድን ናቸው?

4. እግዚአብሔር ለማያቋርጥ አለመታዘዛቸው እስራኤላውያንን ይቅጣል (ኢሳ. 43፡22–28 አንብብ)

ኢሳይያስ ለአይሁዶች በፈቃደኝነት በእግዚአብሔር ላይ የፈጸሟቸው አለመታዘዞች የሚያስከትሏቸውን መዘዞች ገልጾላቸዋል። እግዚአብሔር እስራኤላውያንን የጠራቸው በቅድስናና በምስጋና በፊቱ እንዲኖሩ ነበር። በሚያቀርቧቸው መሥዋዕቶች ምስጋናቸውን በመግለጽ በአምልኮአቸው ሊያስከብሩት ይገባ ነበር። ነገር ግን ሌላ ነገር ሆነ።

1. አይሁዶች እግዚአብሔርን ተዉት። ኢሳይያስ ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ምንም እንኳ አይሁዶች መሥዋዕቶችን በማቅረብ እግዚአብሔርን የማምለኩን ሂደት ባያቋርጡም፥ ሕይወታቸው ለእግዚአብሔር በታዛዥነት እንዳልተሰጠ ነው። ስለሆነም እነዚህ መሥዋዕቶች ምንም ትርጉም ያልነበራቸው በመሆኑ እግዚአብሔር የሚመለከተው መሥዋዕት እንዳልቀረበለት ያህል ነበር። በእግዚአብሔር እይታ፥ ከአምልኮና ውዳሴ ልብ ያልፈለቀ ሥርዓት እንደ አምልኮ ሊቆጠር አይችልም። (በተሳሳተ አመለካከት ስለሚቀርብ አምልኮ ሚልክያስ 1፡6–7 ተመልከት።)

ወይም ደግሞ ለእግዚአብሔር ግድ የማይሰኝ መንፈስ ሰፍሮባቸው ይሆናል። ስለ እርሱ ከማሰብ፥ ወደ እርሱ ከመጸለይ ወይም እርሱን ከማምለክ ተቆጥበዋል። ለእግዚአብሔር ልጅ ለአምላኩ የሚገባውን ክብርና ትኩረት ለመስጠት እስከማይችልበት ደረጃ ድረስ ግድ የለሽ ወይም ሥራ ብዙ ከመሆን የበለጠ ኃጢአት የለም። አይሁዶች እጅግ ሥራ ብዙ ወይም ግድ የለሽ በመሆናቸው ምክንያት ያቀርቡለት ዘንድ ያዘዛቸውን መሥዋዕቶች አላቀረቡለትም። እነዚህም ለኃጢአታቸው

ሙሉውን እንስሳ የሚያቀርቡበት የሚቃጠል መሥዋዕት፥ ጉድለታቸውን ሁሉ እንደሞላላቸው በመግለጽ የሚያመሰግኑበት የእህል ቁርባን፥ የጸሎትና የምስጋና ምልክት ሆኖ ከመሥዋዕቶች ጋር የሚቀርበው ዕጣንና ሁልጊዜም ለእግዚአብሔር ሊቀርብ የሚገባው ስብ ማለትም የእንስሳው ዋነኛ አካል ነበር። እግዚአብሔር ምስጋናውን በአነስተኛ ነገር እንዲገልጹለት እንጂ ብዙ መሥዋዕቶችን እንዲያቀርቡለት አልጠየቀም ነበር። ያንንም እንኳ አላሟሉም። አይሁዶች አመስጋኝነታቸውን ለመግለጽ ከብዛቱ የተነሣ እግዚአብሔርን የሚያታክት መሥዋዕት ማቅረብ ነበረባቸው። ነገር ግን እግዚአብሔርን ከልባቸው ስለማይወዱት እርሱን ለማገልገል ሊደክሙ አልፈለጉም። ምርታቸውን ወይም ራሳቸውን በውዳሴ፥ በምስጋና፥ በአምልኮና በአገልግሎት ይሰጡት ዘንድ እግዚአብሔር ብዙም ለእነርሱ አስፈላጊ አልነበረም።

9ኛ ጥያቄ፦ ሀ) ዛሬ ይኸው ተመሳሳይ አመለካከት በብዙ ክርስቲያኖች ሕይወት የሚታየው እንዴት ነው? ለ) እንዲሁ ከመዘመርና «ሃሌሉያ» እያሉ ከማዜም በተጨማሪ ለእግዚአብሔር ያለንን ፍቅር የምንገልጽባቸውን መንገዶች ዘርዝር።

2. በእግዚአብሔር ላይ በግልጽ ዐመፁ። እግዚአብሔርን በብዙ መሥዋዕቶቻቸው እንደማድከም በብዙ ኃጢአቶቻቸው ያሰለቹት ጀመር። የሕዝቡ ኃጢአት ለእግዚአብሔር በአህያ ላይ እንደተጫነ ሸክም ከበደ።

ለብዙ ምእተ ዓመታት እግዚአብሔር መተላለፋቸውን ይቅር ሊላቸው ቆይቷል። በዕብራይስጥ ይህ ቃል የተጻፈውን የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ለመጠበቅ አለመቻልን ያመለክታል። እግዚአብሔር ብዙ ጊዜ ኃጢአታቸውን ይቅር ብሎላቸዋል። እግዚአብሔር ከልባቸው ንስሐ ከገቡ አሁንም የሕዝቡን ኃጢአት ይቅር ለማለት ዝግጁ ነበር። እነርሱ ግን ንስሐ አልገቡም።

ስለሆነም ለኃጢአታቸው ፍርድን የሚቀበሉበት ጊዜ ደረሰ። ኢሳይያስ አሁንም ወደ ፍርድ ችሎት ትእይንቱ ተመለሰ። ቀደም ሲል እግዚአብሔር አሕዛብን ጣዖቶቻቸው ምን ያህል ከንቱዎች እንደሆኑ በመግለጽ አጋፍጦአቸዋል። አሁን ደግሞ ኮብላይ ሕዝቡን ጠርቶ ለምን እንደማይቀጣቸው ጠይቆአቸዋል። ንጹሐን መሆናቸውን፥ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት በታማኝነት እንደጠበቁና ሕይወታቸውን በምስጋናና በአገልግሎት እንደሚመሩ ማረጋገጥ ነበረባቸው። ነገር ግን ንጽሕናቸውን ሊያሳዩ አልቻሉም ነበር። ከፊተኛው አባታቸው (ምናልባትም አብርሃም ወይም አዳም ወይም ያዕቆብ) እስከነበሩበት

ትውልድ ድረስ አይሁዶች ኃጢአት የመሥራት ባሕል አዳብረው ነበር። የተሻለ እውቀት ሊኖራቸው የሚገባቸው መምህሮቻቸው ማለትም ካህናትና ነቢያት ሳይቀሩ እንደተቀረው ሕዝብ ሁሉ ኃጢአተኞች ነበሩ። የሚያሳዝነው የእስራኤልን ታሪክ ስንመለከት ሕዝቡ ምሳሌያዊ ሕይወት የኖረበት ጊዜ በጣም አጭር መሆኑ ነው። ታሪካቸው ማለቂያ በሌለው ኃጢአት ተለይቶ ይታወቃል።

የይቅርታ ጊዜ ተሟጥጦ የፍርድ ሰዓት ደረሰ። እግዚአብሔር መንፈሳዊ መሪዎች ሊሆኑ የሚገባቸውን የመቅደሱን አለቆች ማለትም ካህናትና ሌዋውያን እንደሚያረክስ ገለጸ። ሕዝቡን ወደ ኃጢአት ስለመሩት የእግዚአብሔር ፍርድ በቀዳሚነት የሚያነጣጥረው በእነርሱ ላይ ይሆናል። ሕዝበ ባቢሎን ወደ ኢየሩሳሌም መጥቶ ቤተ መቅደሱን ባፈረሰበት ጊዜ በቀዳሚነት ከተገደሉት ወይም ወደ ምርኮ ከተሰደዱት መካከል ካህናት ይገኙ ነበር። እግዚአብሔር ይሁዳ በባቢሎን መውደም እንዳለባት በቁርጠኝነት ወስኖ ነበር። ኢሳይያስ ማፍረስን ለመግለጽ የተጠቀመው ቃል ኢያሱ ኢያሪኮን ሙሉ ለሙሉ ያወደመበትን ሁኔታ ለመግለጽ ካገለገለው ጋር አንድ ነው። ይህም አንድን ነገር ለእግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ መደምሰስን ያመለክታል። ከኃጢአቷ የተነሣ እግዚአብሔር እስራኤልን ቀደም ሲል እርሷ የአሕዛብን አገሮች ባወደመችበት መንገድ ያወድማት ነበር።

10ኛ ጥያቄ፦ ሀ) የእስራኤል ታሪክ ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ለ) ለእግዚአብሔር ያለንን መንፈሳዊ ፍቅር መጠበቅ የሚከብደን ለምንድን ነው? ሐ) እግዚአብሔር ከሕዝቡ ኃጢአት የተነሣ ከአንዲት ቤተክርስቲያን በረከቱን የሚነሣበትና ጀርባውን የሚሰጥበት ጊዜ የሚመጣ ይመስልሃል? መልስህን አብራራው። መ) የዚህን ምዕራፍ መንፈሳዊ በረከት ጠቅለል አድርገህ ግለጽ።

ሁለተኛ ቀን ኢሳይያስ 44

አንድ ቀን ጌታሁን በአካባቢው ጉባዔ ስለሚያካሂድ አዲስ ቡድን የሚነገር ወሬ ሰምቶ ወደዚያው ለመሄድ ወሰነ። ተናጋሪው በአካባቢው በፍልስፍና ችሎታው የተደነቀ ሰው ነበር። ይህ ሰው ስለ ሰው ክብር እየተናገረ፥ «እኛ ሁላችንም አማልክት ነን። መለኮታዊ ኃይል ለማግኘት ልናደርግ የሚገባው ነገር ቢኖር ወደ ውስጣችን መመልከት ብቻ ነው። በተመስጦ መንፈስ ውስጥ ብንሆን መለኮታዊ ባሕርያችን መጥቶ ራሳችንንና በአካባቢያችን ያሉትን ሁሉ የምንቆጣጠርበትን የአማልክትን ኃይል ይሰጠናል። መለኮታዊ ኃይል እንጨብጣለን» አለ። ሰዎቹ እግሮቻቸውን እንዴት እንደሚያጣምሩ፥ ዓይኖቻቸውን እንዴት እንደሚጨፍኑና አንዳንድ ጥንታዊ ቃላትን እንዴት

እንደሚናገሩ አሳያቸው። ሰዎቹ በተመስጦ መንፈስ ውስጥ ሲሆኑ ሰላም ተሰማቸው። ጌታሁን የማይመጠን ኃይል ያለው አምላክ መሆኑን ሲሰማ ተደሰተ። ጌታሁን በትምህርት ቤት ጥሩ ውጤት ለማምጣት፥ የሚያፈቅራት ልጃገረድ እንድትወደው ለማድረግ፥ ወዘተ... ይህንን ልዩ ኃይል ፈለገ። ብዙም ሳይቆይ ጌታሁን የዚህ «ኒውኤጅ» የተባለው አዲስ ሃይማኖት ተከታይ ሆነ።

ናምሩድ ለጎሳው ቡድን ታማኝነቱን ለማሳየት የሚፈልግ የተማረ ሰው ነበር። አንድ ቀን በፖለቲካ ስብሰባ ወቅት የስብሰባው መሪ፥ «ጎሳችንን ማክበር ካለብን ጥንታዊ የባሕል አምልኮአችንን መከተል አለብን። ከወንዙ አጠገብ ወዳለው የዋርካ ዛፍ በመሄድ በዚያ ለሚኖሩት መናፍስት እንስሳትን በመሠዋት ልናመልክ ይገባል። ለእነዚህ አማልክት የታማኝነታችንን ተምሳሌት ማቅረብ አለብን። ጥንታዊ ቅርሳችንን የምናከብረው በእንዲህ ዓይነቱ መንገድ እንጂ እንደ ክርስትና ዓይነቶቹን አዳዲስ ሃይማኖቶች በመከተል አይደለም» ሲል ተናገረ። ናምሩድ ለጎሳው ታማኝነቱን ለማሳየት ስለፈለገ ከቡድኑ ጋር ወደ ዛፉ በመሄድ የእንስሳት መሥዋዕት የታከለበትን ባዕድ አምልኮ አካሄደ።

11ኛ ጥያቄ፦ ኢሳይያስ 44፡6-20 አንብብ። ሀ) ይህ ክፍል ለጌታሁንና ናምሩድ የሚሰጠው ምክር ምን ይመስልሃል? ለ) ሰዎች ወደ አዳዲስ ወይም ጥንታዊ ሃይማኖቶች የሚሳቡት ለምን ይመስልሃል? ሐ) ዛሬ ብዙዎች ሰዎች በኢትዮጵያ ውስጥ በዚህ ዓይነቱ መንገድ የሚፈተኑት እንዴት ነው?

ሰይጣን ሁልጊዜም በዓለም ውስጥ ሰዎች እውነት መሳይ ሃይማኖቶችን እንዲከተሉ ለማድረግ በመጣር ላይ ይገኛል። በመጀመሪያ፥ ሰይጣን እግዚአብሔር የከለከለውን ዛፍ ከበላች አምላክ እንደምትሆን በመናገር ሔዋንን አሳሳተ። የተፈጠረ ሰው ፈጣሪ አምላክ ይሆናል ብሎ ማሰብ ምንኛ ሞኝነት ነው! በሮሜ 1፡18-23 ሰው እንደ ዛፍ ዓይነቶቹን የተፈጠሩ ነገሮች ለማምለክ ሲል ፈጣሪ አምላኩን ከማምለክ እንደተቆጠበ ተገልጾአል።

አይሁዶች ወደ ምርኮ ሲሄዱ፥ የተለያዩ አማልክትንና ጣዖታትን የሚያመልኩትን አሕዛብ ልማድ የመከተል ፈተና ይጋረጥባቸው ነበር። ሁሉም ሰው ጣዖታትን እያመለከ ለአይሁዶች የማይታየውን ፈጣሪ በማምለክ ተነጥሎ መታየቱ ከባድ ነበር። እግዚአብሔር የነገሩን ከንቱነት ለማሳየት ሲል ጣዖታት እንዴት እንደሚሠሩ በሥዕላዊ ገለጻ አስተማራቸው።

12ኛ ጥያቄ፦ ኢሳይያስ 44ን አንብብ። ሀ) ከቁጥር 1-2 እግዚአብሔር ስለ እስራኤል የሰጠውን ገለጻ ዘርዝር። እያንዳንዱ ገለጻ አይሁዶችን የሚያጽናናው

እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር ለእስራኤል አደርጋለሁ ያላቸውን ነገሮች ዘርዝር። ሐ) እነዚህ ነገሮች በሚፈጸሙበት ጊዜ አይሁዶች ለእግዚአብሔር ታማኝነታቸውን የሚያሳዩት እንዴት ነው? መ) ከቁጥር 6–20 እግዚአብሔር ለአይሁዶች የሚያስተላልፈውን መልእክት ጠቅለል አድርገህ አቅርብ። ሠ) ከቁጥር 21–22 እግዚአብሔር ለሕዝቡ እንደሚያደርግ የተናገረው ምንድን ነው? ረ) ከቁጥር 24–28 ስለ እግዚአብሔርና ስለሚያከናውናቸው ተግባራት የተሰጠውን ገለጻ ጠቅለል አድርገህ አቅርብ። ይህ በምርኮ ላሉት አይሁዶች ትልቅ መጽናኛ የሚሆነው ለምንድን ነው?

1. እግዚአብሔር የመረጣቸውን እስራኤላውያንን በመለወጥ እርሱን እንዲመርጡት ያደርጋል (ኢሳ. 44፡1–5 አንብብ)

የእስራኤል ታሪክ የኃጢአትና የዓመፅ ታሪክ ነበር። ይህም የኋላ ኋላ የእግዚአብሔር ምድራዊ ዙፋን የሚገኝበትን ቤተመቅደስና ኢየሩሳሌምን ሙሉ ለሙሉ አወደማቸው። ነገር ግን ይህ ሁኔታ ሁልጊዜም ይቀጥል ይሆን? የእግዚአብሔር ሕዝብ ይለወጡ ይሆን? አዎ፤ ኢሳይያስ አንድ ቀን እግዚአብሔር ነገሮችን በመቀየር የሕዝቡን ልብ ይለውጥና እርሱን እንዲከተሉት ያደርጋቸዋል ብሏል።

በባቢሎን ምርኮ ሳሉ አይሁዶች አሁንም የእግዚአብሔር ልዩ ሕዝብ መሆናቸውን መጠራጠራቸው አይቀርም። ኃጢአታችን ቅጥ ያጣ በመሆኑ እግዚአብሔር ከእንግዲህ ለእኛ ምንም ዕቅድ የለውም ብለውም ይሆናል። እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር ያለው ግንኙነት እንዳልተቋረጠ በብዙ የተለያዩ መንገዶች አመልክቷል። (ማስታወሻ፡ እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለውን ግንኙነት በአጽንኦት ለመግለጽ እነዚህን ስሞች ደጋግሞ ጠቅሶአል።)

ሀ. አይሁዶች አሁንም የእግዚአብሔር ባሪያዎች ነበሩ። ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ባሪያ መሆን ሁለት ገጽታዎች አሉት። የራሱ ነጻነት የሌለውን ሰው ሊያመለክት ይችላል። ሕዝቡ የእርሱ ባሮች ስለሆኑ እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ሙሉ መብት ነበረው። ቃሉ በዚህ ስፍራ የተጠቀሰው ግን ከእርሱ ጋር የተለየ ግንኙነት እንዳላቸው ለማመልከት ነው። በጥንት ዘመን ከንጉሡ ጋር የቅርብ ግንኙነት ኖሮት የንጉሡን ጉዳይ ለመፈጸም ለተለየ ተልእኮ ወደ ሌላ ስፍራ የሚሄድ አምባሳደር የንጉሡ ባሪያ እንደሆነ ይነገር ነበር። እንዲሁም እግዚአብሔር እስራኤልን ለዓለም አምባሳደሩ አድርጎ መርጦአታል።

ለ. እግዚአብሔር መርጦአቸዋል። አንድን ነገር ስትመርጥ ከሌሎቹ ትለየዋለህ። ወደ ልብስ መደብር ብትሄድ እዚያ ከሚገኙት ሁሉ የሚስማማህን መርጠህ ትገዛለህ። ያም ልብስ ለአንተ ከእነዚያ ልብሶች ሁሉ የተለየ ይሆናል። እግዚአብሔርም እስራኤልን ከዓለም ሕዝቦች

ሁሉ መርጦአታል (ዘጸ. 19፡3–6)። ስለሆነም እስራኤል እንደ ዋዛ ልትጣል የምትችል ሳትሆን ለእግዚአብሔር ልዩ ነበረች።

ሐ. የፈጠራቸው እግዚአብሔር ነው። አንድ ሠዓሊ አንድን ምስል በሚሠራበት ጊዜ ምስሉ ለእርሱ ልዩ ነው። አንድ አናጺ በእጁ የሠራውን ጠረጴዛ ከገበያ ከገዛው እኩል አያየውም። በተመሳሳይ ሁኔታ እግዚአብሔር እስራኤልን የራሱ ሕዝብ አድርጎ ስለፈጠረ ከእርሱ ጋር ልዩ ግንኙነት ማድረጋቸው ይቀጥላል።

መ. እግዚአብሔር በማኅፀን ሳሉ ሠርቶአቸዋል። በመዝሙር (139)፡13–16 ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር የተለየና የቀረበ ግንኙነት ስለነበረው፥ እግዚአብሔር በእናቱ ማኅፀን ውስጥ ተገኝቶ የተለያዩ አካላቱን በማገጣጠምና ልዩ ስብዕና በማጎናጸፍ ሰው አድርጎ እንደሠራው የሚያስመስል ገለጻ አቅርቦአል። (ማስታወሻ፡ እግዚአብሔር ውርጃን አጥብቆ ከሚጠላባቸው ምክንያቶች አንዱ ይኼ ነው። ሕጻኑን በእናቱ ማኅፀን ውስጥ ለመቅረጽ ልዩ ጥንቃቄ ስለሚያደርግ ያንን ለማስቆም መጣሩ ከነፍሰ ገዳይነት እኩል ነው። አንድ ሰው ሳይፈለግ የተረገዘውን ልጅ ከተወለደ በኋላ ቢገድለውም ያው ነፍሰ ገዳይነት ነው።) የልጅን መወለድ ምሳሌ በመጠቀም እግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር ያለው ግንኙነት እጅግ የቀረበ እንደሆነና አይሁዶችን ልዩ ኅብረት እንደሚያደርግባቸው ሕዝብ አድርጎ እንደሠራቸው ገልጾአል።

ሠ. እስራኤል ይሹሩን ተብሎ ተጠርቶአል። ይህ ለእስራኤል የተሰጠው ስም ከዚህ በተጨማሪ የተጠቀሰው በዘዳግም 32፡15 (33፡5፥ 26) ብቻ ነው። ይሹሩን ማለት ቀጥተኛው፥ ትክክለኛው ማለት ነው። (ይህም «አታላይ» የሚል ፍች ካለው ያዕቆብ የሚቃረን ነው።) በዘዳግም ይህ ስም እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያለውን ተስፋ ያመለክታል። እግዚአብሔር ሕዝቡን የጠራው ቅዱስ፥ ፍትሐዊ፥ ትክክለኛና ከሌሎች የዓለም ሕዝቦች ሁሉ እንደሚለዩ ተስፋ በማድረግ ነበር። ነገር ግን ከባረካቸው በኋላ ዓመፁበት። አሁንም ወደፊት እስራኤላውያንን የሚባርክበትን ጊዜ አሻግሮ እየተመለከተ አይሁዶች በስም ብቻ ሳይሆን በተግባርም ይሹሩን እንደሚሆኑ ያስባል። የሕዝቡ ልብ ይለወጥና የእግዚአብሔርን ሕግጋት ይከተላሉ።

13ኛ ጥያቄ፡– ሀ) እነዚህ ገለጻዎች ለክርስቲያኖችም እውነት የሚሆኑት እንዴት ነው? ለ) እነዚህ እውነቶች ክርስቲያኖች በአስቸጋሪ ጊዜያት ሳይቀር በዓለም ውስጥ የሚከሰቱትን ነገሮች እንዳይፈሩ የሚያበረታቷቸው እንዴት ነው?

ረ. እግዚአብሔር ይረዳቸዋል። እግዚአብሔር ሕዝቡ በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ውስጥ በሚሆኑበት ጊዜ የሚረዳቸው ከእነርሱ ጋር ባለው ግንኙነት መሠረት ነው። እግዚአብሔር እስራኤልን ስለመረጠ (እስራኤል ከእግዚአብሔር ጋር ግንኙነት ለማድረግ አልመረጠችም) በልዩ መንገዶች ሊረዳቸው ቃል ገባ።

1. ለምድራቸው ውኃን ይሰጣቸዋል። (ማስታወሻ፡ ለደረቅ ምድር ወይም ለምድረ በዳ ውኃ የመስጠቱ ተስፋ በትንቢተ ኢሳይያስ ውስጥ ተደጋግሞ የተጠቀሰ አሳብ ነው [ኢሳ. 30፡25፤ 32፡2፤ 35፡6–7።] የከነዓን ምድር እንደ አብዛኛው ሰሜን ኢትዮጵያ ደረቅ በመሆኑ ውኃ እንደ አንድ ልዩ ነገር የሚታይ ነበር። በይሁዳ ብዙውን ጊዜ ሰዎች ከዝናብ እጥረት ሳቢያ ድርቅ ያጠቃቸው ስለነበር፥ ኢሳይያስ እስራኤልን ከተጠማ ሰው ጋር አነጻጽሮአታል። እግዚአብሔር ከበረከቶቹ እንደ አንዱ አድርጎ ብዙ ውኃን በዝናብ ብቻ ሳይሆን በወንዞች እንደሚልክ ተናግሮአል። በሌላ አገላለጽ፥ እግዚአብሔር በረከቶቹን በሕዝቡ ላይ በማፍሰስ ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቻቸውን ያሟላል ማለት ነው።

2. እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ መንፈሱን ያፈስሳል። ቀደም ብለን በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር *መንፈስ መሢሑ* ከሚያመጣቸው በረከቶች ጋር በቅርብ የተዛመደ መሆኑን ተመልክተናል (ኢሳ. 32፡15፤ ኢዩ. 2፡28)። እግዚአብሔር መንፈሱን ለመሢሑ እንደሚሰጥ ሁሉ (ማቴ. 3፡16)፥ በሕዝቡ ሁሉ ላይም ያፈስሳል። የብሉይ ኪዳን አይሁዶች ይህንን አሳብ እግዚአብሔር እንደ ሳምሶን ላሉት መሪዎች እንደሰጠው የመንፈስ ቅዱስ የማስቻል ኃይል አድርገው ከመረዳት ይልቅ እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱሱን ለተመረጡት መሪዎች ብቻ ሳይሆን ለሕዝቡ ሁሉ በመስጠት እንደ ፈቃዱ ቃሉን ታዝዘው ሊሰጣቸው የሚፈልገውን በረከት እንዲቀበሉ የሚያደርግ መሆኑን ተገንዝበዋል። ይህ ምንባብ እግዚአብሔር እርሱን በመታዘዝ ይመላለሱ ዘንድ ለክርስቲያኖች ሁሉ መንፈስ ቅዱስን በሰጠበት በቤተ ክርስቲያን ተፈጽሞአል። ሙሉ ለሙሉ የሚፈጸመው ግን ወደ ፊት የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ መላው የእግዚአብሔር ሕዝቡ ሙሉ ለሙሉ እንዲታዘዙትና እንዲያከብሩት ልባቸውን በሚለውጥበት ወቅት ነው።

3. እግዚአብሔር በዘሮቻቸው ላይ መንፈሱን ያፈስሳል። መጽሐፍ ቅዱስ መንፈሳዊ ወላጆች በልጆቻቸው ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩ ያስተምራል። ክርስቲያን ወላጆች ያሏቸው ልጆች እግዚአብሔርን ለመከተል እንደሚመርጡ የሚያረጋግጥ ዋስትና የለም። እያንዳንዱ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስን ለመከተል ወይም

ላለመከተል ግላዊ ውሳኔ ማድረግ እንዳለበት መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምራል (ሕዝ. 18)። ክርስቲያን ወላጆች ልጆቻቸው እንዴት የእግዚአብሔር ቤተሰብ አካል ሊሆኑ እንደሚችሉ በጥንቃቄ ማስተማር ያለባቸው ለዚህ ነው። በታሪክ ሁሉ የሚታየው አጠቃላይ ዝንባሌ ክርስቲያን ወላጆች ያሏቸው ልጆች የወላጆቻቸውን ያህል ጠንካራ እምነት እንደማይኖራቸውና ሦስተኛው ትውልድ በእግዚአብሔር ላይ እንደሚያምፅ ነው። (ለምሳሌ፥ ዳዊትን፥ ሰሎሞንና ሮብዓምን መመልከት ይቻላል።) ኢሳይያስ ግን የእግዚአብሔር በረከት ከአንዱ ትውልድ ወደ ሌላው ስለሚፈስበት ዘመን ተናግሮአል። እግዚአብሔር የሰዎችን ልብ በመለወጥ ትውልዶች ሁሉ እርሱን እንዲታዘዙት ያደርጋል።

እግዚአብሔር በሚታዘዙት ትውልዶች ላይ የሚያወርደውን በረከት ከሣሮችና ከውኃ ዳር ከሚበቅሉ የአኻያ ዛፎች ጋር አነጻጽሮአል። ሣር በጣም ፈጥኖ ከማደጉም በላይ አመርቂ ፍሬን ይሰጣል። የአኻያ ዛፍ ቶሎ የሚያድግ ነው። በመሆኑም የእግዚአብሔር በረከት ሰዎች ብዙ ልጆች እንዲወልዱ ብቻ ሳይሆን፥ ልጆቹ በጤንነት አድገው ወላጆቻቸውን ደስ እንደሚያሰኙ ያመለክታል። በብሉይ ኪዳን ከሚታወቁት የበረከት ተምሳሌቶች አንዱ ብዙ ልጆችና የልጅ ልጆችን መውለድ ነበር።

በኢያሱ የአንድ ትውልድ ሕዝብ እግዚአብሔርን እንደተከተሉና ትውልዱ ካለፈ በኋላ የመጡት ግን እግዚአብሔርን እንደዘነጉት ተገልጾአል (ኢያሱ 24፡31፤ መሳ. 2፡7፥ 10–15)። ይህ ሁኔታ ግን በመጨረሻው ዘመን ይለወጣል። ልጆች የወላጆቻቸውን ያህል እግዚአብሔርን ይወዱታል። እርሱን ለመከተል ይመርጣሉ። የእግዚአብሔር መሆናቸውን ለማመልከት፥ በእጆቻቸው ላይ «እኔ የእግዚአብሔር ነኝ» ብለው ይጽፋሉ። ከአሕዛብ አማልክት ጋር ከመተባበር ወይም ዛሬ ብዙ አይሁዶች እንደሚያደርጉት አይሁዳዊ ቅርሳቸውን ከመክዳት ይልቅ በግልጽና በፈቃደኝነት በያዕቆብ ወይም በእስራኤል ስም ይጠራሉ። በአይሁድ ባሕል፥ በአዲስ ስም መጠራት አዲስ ሁኔታ እንደተፈጠረና አዲስ ግንኙነት እንደተከሰተ ያመለክታል። ይህ ሁኔታ ይለወጥና ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸው ግንኙነት እስራኤልን የራሱ ሕዝብ አድርጎ በመረጠበት ጊዜ እንደፈለገው ዓይነት ይሆናል።

14ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ሰዎች ለእግዚአብሔር ያላቸው አመለካከት ከትውልድ ትውልድ እየቀነሰ የመሄዱን እውነት እንዴት እንደታዘብህ ግለጽ። ለ) የቤተክርስቲያን መሪዎች ልጆቻቸውና ወጣቱ ትውልድ የደኅንነትን መንገድ እንዲያውቁና እግዚአብሔርን ለመከተል በግላቸው እንዲመርጡ ለማድረግ

ሊወስዱቸው የሚገባቸው እርምጃዎች ምንድን ናቸው? ሐ) አንድ ልጅ በስንት ዓመቱ በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን የሚችል ይመስልሃል? ለመልስህ ምን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ አለህ? መ) ብዙ ክርስቲያኖች ከአሥር ዓመት በታች የሚገኙ ልጆች በኢየሱስ ክርስቶስ ለማመን እንደማይችሉ ያስባሉ። እንደዚህ ብለው የሚያምኑት ለምንድን ነው? ይህንን አሳብ የሚያፈርስ ምን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማረጋገጫ አለ?

2. ለደኅንነትና ለአምልኮ ወደ ጣዖታት የማዘንበል ከንቱነት (ኢሳ. 44፡6–23)

መምህራን «ድግግሞሽ የትምህርት እናት ነው» ሲሉ ይሰማል። በሌላ አገላለጽ፥ አንድ ሰው አንድን ጠቃሚ እውነት እንዲይዝ ከተፈለገ በተደጋጋሚ ሊነገረው ይገባል ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እግዚአብሔር ሕዝቡ እንዲከተላቸው የፈለጋቸውን ቃላት ወይም አሳቦች በተደጋጋሚ ጠቅሷቸዋል። ከኢሳይያስ 40–48 በተደጋጋሚ ከተጠቀሱት አሳቦች አንዱ ከፈጣሪ አምላክ ጋር ሲነጻጸሩ ጣዖታት ምን ያህል ደካሞች እንደሆኑ የሚያሳየው ነው። በምርኮ የነበሩት አይሁዶች ጣዖታትን ለማምለክ በከፍተኛ ደረጃ ስለሚፈተኑና እምቢ ካሉም በአሕዛብ ስለሚሰደዱ ቀደም ብለው ትምህርት ማግኘታቸው ወሳኝ ነበር። በዚህ ክፍል ኢሳይያስ እግዚአብሔር ማን እንደሆነና ጣዖታት ምን እንደሆኑ በማነጻጸር ገልጾአል።

ሀ. የእስራኤል አምላክ ታላቅነት (ኢሳ. 44፡6–8 አንብብ)

1. የእግዚአብሔር ታላቅነት በስሞቹ ተገልጾአል (ኢሳ. 44፡6)። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ስም በተደጋጋሚ ተጠቅሶ እናነባለን። ብዙዎቻችን ጠቃሚው ነገር የእግዚአብሔር ስም እንደሆነ እናስባለን (ለምሳሌ ያህዌ፥ ኤልሻዳይ)። ብዙ ክርስቲያኖች የእነዚህን ሐረጎች ፍች በተሳሳተ መንገድ ይረዳሉ። የኢየሱስን ስም ጮክ ብለው ከጠሩ የበለጠ ኃይል እንደሚኖረው ያስባሉ። መጽሐፍ ቅዱስ ግን ስለ እግዚአብሔር ወይም ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ስም በሚናገርበት ጊዜ ለማስተላለፍ የፈለገው መልእክት ይኼ አይደለም። ለአይሁዶች ስም የተጠሪውን ሁለንተናዊ ባሕርይ ወይም ኑባሬ ያመለክታል። ስለሆነም እግዚአብሔር ከባሕርያቱ አንዱን ለመጥቀስ ሲፈልግ ያንኑ ባሕርይ በስም ይገልጸዋል። ለምሳሌ እግዚአብሔር ራሱን «ያህዌ ይርኤ» ብሎ ሲጠራ ሊያስተላልፍ የፈለገው መልእክት በስሙ ላይ ትኩረት ማድረግ ሳይሆን ሕዝቡ እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን የሚያሟላላቸው አምላክ እንደሆነ እንዲገነዘቡ ነው። እግዚአብሔር ሰጭ አምላክ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ በኢየሱስ ስም ስንጸልይ ስሙ ምትሐታዊ ኃይል እንዳለው ማሰባችን አይደለም። ይልቁንም ጸሎቱን

የምናቀርብበት ሥልጣን በኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነትና እኛ የእርሱ ተከታዮች እንደመሆናችን ባለን ግንኙነት ላይ የተመሠረተ መሆኑን በይፋ የምንገልጽበት ነው።

ለእስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለማሳየት ኢሳይያስ ብዙ ስሞችን ዘርዝሮአል። እነዚህ የእግዚአብሔር ስሞች ባሕርዩን በመግለጽ አይሁዶች ወደ ጣዖታት ሳያዘነብሉ በእግዚአብሔር ጸንተው እንዲኖሩ የሚያደርጓቸው ነበሩ።

ሀ. *የእስራኤል ንጉሥ።* ኢሳይያስ አይሁዶች ከአገራቸው ውጭ ሲኖሩ በትንቢታዊ ዓይኖቹ ተመለከተ። ጥንታዊው የዳዊት ንጉሣዊ ሐረግ ለተወሰነ ጊዜ ይቋረጣል። ይሁንና፥ እግዚአብሔር አሁንም በሕይወታቸውና በሚያጋጥማቸው ሁኔታ ሁሉ ላይ ፍጹማዊ ሥልጣን ያለው ንጉሣቸው ነበር። የእግዚአብሔር ንግሥና በአካላዊ ድንበሮች የተገደበ ሳይሆን መንፈሳዊም ነው። እግዚአብሔር እንደ መንፈሳዊ ንጉሥ የሚገዛ አምላክ በመሆኑም ነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለአይሁዶች የእግዚአብሔር መንግሥት በመካከላቸው እንደሆነች የተናገረው (ማቴ. 12፡28፤ ሉቃስ 10፡9)።

ለ. *ተቤዥ።* እግዚአብሔር አይሁዶችን ከግብፅ ባርነት ያወጣቸው አምላክ እንደመሆኑ፥ ከባቢሎንም ባርነት የሚያወጣቸው እርሱ ነበር። ከመንፈሳዊና ፖለቲካዊ ባርነት ያወጣቸው ዘንድ ባለማቋረጥ ወደ እግዚአብሔር መመልከት ነበረባቸው – በባሕርዩ እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ ተቤዥ ነውና። እርሱ ነፃ ሊያወጣ ከወሰነ ማንም ሊያስቆመው አይችልም።

ሐ. *ሁሉን የሚችል አምላክ።* እግዚአብሔር በኃይላት ሁሉ ላይ ሙሉ ሥልጣን ያለው ሉዓላዊ ገዥ ነው። ይህም እንደ ሰይጣን እና አጋንንት ያሉትን መንፈሳዊ ኃይላትና እንደ አገሮችና ነገሥታት ያሉትን አካላዊ ኃይላት የሚያካትት ነው። ስለዚህ ለሕዝቡ የሚያከናውነውን ተግባር ሊገታ የሚችል ማንም የለም።

መ. *የመጀመሪያውና የመጨረሻው።* በሰው ምናባዊ ፈጠራ ከሚሠሩት ጣዖታት በተቃራኒ እግዚአብሔር ሁልጊዜም ያለና የሚኖር አምላክ ነው። ከዘመናትና ከፍጥረት ሁሉ በፊት እግዚአብሔር ነበር። ከእግዚአብሔር ቀድሞ የተገኘ ነገር አልነበረም። እንዲሁም ደግሞ ሁሉም ካለፈ በኋላ እግዚአብሔር ይኖራል። ሰው–ሠራሽ አማልክትና ጣዖታት ሁሉ ይበሰብሳሉ ወይም ከጊዜ ወደ ጊዜ የሰዎች አሳብ ሲቀየር ይለወጣሉ። ሕያው አምላክ ግን ሳይለወጥ በዘመናት ሁሉ ይኖራል። ስለሆነም አይሁዶች እነርሱ በይሁዳ ምድር ባለመኖራቸው አምላካቸው እንደሌለ አድርገው ሊያስቡ

አይገባቸውም ነበር። እግዚአብሔር ሁልጊዜም የቃል ኪዳን ግንኙነቱን በመጠበቅ በስፍራው ይኖራል።

ሠ. ከእኔ በቀር አምላክ የለም። እግዚአብሔር ስለ ራሱ የሰጠውን ገለጻ ፈጽሞ በማያሻማ ዓረፍተ ነገር ደምድሟል። ከእርሱ በቀር ሌላ አምላክ አልነበረም። የአሕዛብ ጣዖታት የሰዎች እጅ ሥራዎች እንጂ በርግጥ አማልክት አልነበሩም። ይህ አሳብ ዛሬ ለብዙ ክርስቲያኖች ጠንካራ ማስጠንቀቂያ ያመጣል። በአሜሪካና በአውሮፓ የሚገኙ ብዙ ሰዎች ወደ እግዚአብሔር *ለመድረስ* የሚያስችሉ ብዙ *መንገዶች* እንዳሉና አንድ ሰው በታማኝነት *መንገዱን* ይዞ ከሄደ እግዚአብሔር አምልኮቱን እንደሚያከብርለት ያስባሉ። ስለሆነም ለሙስሊም፥ ለሒንዱ፥ ለቡዲስት ወይም ለባሕላዊ አምልኮ አራማጅ ስለ እግዚአብሔር ያለው አመለካከት የተሳሳተ እንደሆነ *መግለጹ* ተገቢ አይደለም ይላሉ። በዚህ ስፍራ ግን እግዚአብሔር እነዚህ ሃይማኖቶች በሰዎች የተፈጠሩ ከንቱ አሳቦች እንጂ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርሱ እንዳልሆኑ ይናገራል።

ጳውሎስ ምንም እንኳ እነዚህ እውነተኛ አማልክት ባይሆኑም ከእነዚህ አሳቦችና ልምምዶች በስተጀርባ *መንፈሳዊ* ኃይል እንዳለ ገልጾአል። እነዚህን አሳቦች ሰዎች እንዲያምኑ የሚያደርግ ኃይል የሚመጣው ከሰይጣን ነውና (1ኛ ቆሮ. 10፡18–21)። ለብዙ አፍሪካውያን ክርስቲያኖችም እግዚአብሔር እውነተኛውን አምላክና ታሪካዊ ጣዖታት ማምለክ እንደማይችሉ ያስጠነቅቃል። እነዚህ ሁሉ ጣዖታት ውሸተኞችና ኃይልን ከሰይጣን የሚቀበሉ ናቸው። ኃይላቸው ግን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ኃይል ይጠፋል። እውነተኛውን አምላክና ሐሰተኞቹን ጣዖታት ለማምለክ መጣሩ በእውነተኛ አምላክ ላይ የሚፈጸም ዓመፅ ነው።

15ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ከእነዚህ የእግዚአብሔር ስሞች ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ ምን እንማራለን? ለ) አይሁዶች ወይም ክርስቲያኖች ሌሎችን አማልክት ማምለክ እንደሌለባቸው እነዚህ ስሞች ጠንካራ ምክንያቶችን የሚያቀርቡት ለምንድን ነው? ሐ) ይህ ትምህርት የጌታሁንና የናምሩድን ችግሮች የሚፈታው እንዴት ነው?

2. የእግዚአብሔር ታላቅነት የወደፊትን ክስተቶች በመተንበይ ችሎታው ታይቷል (ኢሳ. 44፡7–8)። እግዚአብሔር እርሱ ብቻ ዘላለማዊ አምላክ በመሆኑ አይሁዶች እርሱን ብቻ ሊከተሉት እንደሚገባ ለማድረግ ከሚረዱት ዐበይት ማረጋገጫዎቹ ወደ አንዱ ተመለስ። የወደፊቱን በከፍተኛ ትክክለኛነት ሊተነብይ የሚችለው እርሱ ብቻ በመሆኑ ከመቶ ዓመታት በኋላ እንኳ በትክክል ይፈጸማል። እግዚአብሔር ቀደም ሲል በተለይም በዘጸአት እንደታየው የሕዝቡን

ታሪክ እንደተቆጣጠረ ሁሉ ወደፊትም ይህንኑ ያደርጋል። ይህ ከሌሎች ጣዖታት ማናቸውም ሊያደርጉት ያልቻሉት ነበር። ይህም እግዚአብሔር የወደፊቱን ሊተነብይ እንደሚችል ብቻ ሳይሆን የወደፊቱን እንደሚቆጣጠርም ጭምር የሚያሳይ ነው። በትንቢተ ኢሳይያስ የተጠቀሱት ነገሮች በሚፈጸሙበት ጊዜ አይሁዶች እግዚአብሔር ወደፊት የሚፈጸሙትን ነገሮች እንደተነበየና ነገሮች ሁሉ ከፍጻሜ እንደደረሱ ይመሰክራሉ። ስለሆነም እግዚአብሔር ለአይሁዶች ምንም የሚፈሩበት ምክንያት እንደሌላቸው አስገንዝቧቸዋል። (ከዚህ ምዕራፍ ዐበይት ጭብጦች አንዱ እግዚአብሔር የወደፊቱን ክስተት የሚቆጣጠር አምላክ ስለሆነ ሕዝቡ ምንም መፍራት እንደሌለባቸው የሚገልጸው ነው።) እግዚአብሔር በችግር ጊዜ ሊደበቁበት የሚችል ዓለት ነበር (ዘዳ. 32፡4፥ 15፥ 30–31)።

ለ. ጣዖታትን የማምለክ ሞኝነት (ኢሳ. 44፡9–20 አንብብ)

1. *መቋሚ፣ ጣዖታትን የሚያመልኩ ሰዎች ከንቱዎች ናቸው* (ኢሳ. 44፡9–11)። ሰዎች የሃይማኖታቸውን ባሕርይ ተግባራዊ ያደርጋሉ። ሃይማኖታቸው በቀልን የሚያደፋፍር ከሆነ ብስጩ እየሆኑ ለጸብ ይነሣሣሉ። ኢሳይያስ ጣዖታትን የአሕዛብ አማልክት ከንቱዎች እንደሆኑ ሁሉ የሚያመልኳቸውም ሰዎች ከንቱዎች እንደሆኑ ገልጾአል። ጣዖታትን የሚሠሩና የሚያመልኩ ሰዎች መንፈሳዊ እውነታዎችን ለመረዳት አይችሉም። አምልኮተ ጣዖት የሰው ልጅ አማልክትን ለመሥራት የሚጥርበት ሂደት ብቻ ሳይሆን አማልክቱ እንዲሆኑለት እንደሚፈልጋቸው አድርጎ የሚሠራበትም ነው። አማልክቱን እንደ ሰው አድርገው ይሠራሉ። በተለይም አናጺዎቹ እነዚህን ተግባራት የሚያከናውኑት እነርሱ በመሆናቸው ሞኞች ነበሩ። ራሳቸው ሰዎች ሆነው መለኮታዊ አምላክ እንደሠሩ ያስባሉ። የፈጠሩት ነገር ጸሎታቸውን ለመስማትና ለመመለስ ኃይል እንደሚኖረው በማሰብ ጸሎት ያቀርቡለታል። እንግዲህ የሐሰት አማልክትንና ጣዖታትን ለመከተል የሚመርጡት ሰዎች መጨረሻ ምን ይሆን? አንድ ቀን የሚሠሯቸውና የሚያመልኳቸው ሁሉ ያፍራሉ። የእግዚአብሔርን ፍርድ ለማስፈጸም ሜዶናውያንና ፋርሳውያን በሚመጡበት ቀን፥ በመጨረሻውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመጣበት ጊዜ ጣዖቶቻቸው ስለማይረዱቸው፥ ኃይልን አጥተው ይጠፋሉ። የሞኝነት ተግባራቸውን በመቀበል ለእውነተኛው አምላክ ይሰግዱና ዘላለማዊ ኩነኔያቸውን ይቀበላሉ።

2. *የአምልኮተ ጣዖት ከንቱነት ምሳሌ* (ኢሳ. 44፡12–20)። ኢሳይያስ በስላቅ በመናገር የአምልኮተ ጣዖትን ከንቱነት አሳይቷል። በጣዖት

ቀረጻ ላይ የተሰማሩት ሁለት ዓይነት ባለሙያዎች እንዳሉ ገልጾአል። የብረት ቀጥቃጮች የብረት ወይም የወርቅ አማልክት የሚሠሩ ሲሆን፥ አምላክ የተባለው ጣዖት ሠሪው ምግብ ሳይመገብ ቀርቶ ቢደክም እንኳ ኃይል ሊሰጠው አይችልም።

ሁለተኛው ዓይነት ሰዎች በብዛት የሚጠቀሙበትን ጣዖት የሚቀርጽ ነው። አናጺው ወጣ ብሎ ጣዖት ለመሥራት የሚያገለግል ትልቅና ጠቃሚ እንጨት ይፈልጋል። የሚፈልገውን እንጨት ሲያገኝ ይቆርጠውና ወደ ቤቱ ያመጣዋል። ከእንጨቱ የተወሰነውን ከፍል ጠርቦ በማስተካከል በሰው መልክ ቀርጾ ያመልከዋል። በቤተመቅደስ ወይም በቤት ጥግ አስቀምጦ ለጣዖቱ መጸለይ ይጀምራል። ጣዖቱ ያድነው ዘንድ ያመልከዋል። የተረፈውን እንጨት ለማባከን ስለማይፈልግ ለማገዶነት ይጠቀምበታል። ጥቂቱን እሳት አንድዶ ለቤት ማሞቂያ ሲያደርገው ቀሪውን ደግሞ ምግቡን ያበስልበታል። በሠራው ጣዖት ፊት ተንበርክኮ ይሰግዳል። የቀረው እንጨት ለማገዶና ለቤት ማሞቂያ ይሆናል። አንድን እንጨት ወስዶ ለማገዶነትና ለአምልኮት መጠቀሙ ሞኝነት ነበር። የጣዖት አምላኪዎች የዚህን ነገር ከንቱነት ለመገንዘብ አለመቻላቸው የሚያስገርም ነው።

ይሁንና፥ ሰዎች እንዲህ ዓይነት ተግባር የሚያከናውኑት ለምንድን ነው? አምልኮተ ጣዖት ከንቱ እንደሆነ የማይገነዘቡት ለምንድን ነው? ሁለት ምክንያቶች አሉ። *በመጀመሪያ ደረጃ* መንፈሳዊ ዓይኖቻቸው፥ ጆሮዎቻቸውና አእምሮዎቻቸው ሁሉ ስለ ተጎዱ በትክክል ሊያስቡ አይችሉም። ይህ ስለ እስራኤልም የተነገረው ተመሳሳይ አገላለጽ ነው (ኢሳ. 42፡18–20)። እስራኤላውያን የእግዚአብሔርን ቃል እያወቁ በመንፈሳዊ ዕውርነታቸው ምክንያት በእግዚአብሔርና በሕግጋቱ ላይ በማመፅ በአምልኮተ ጣዖት ራሳቸውን አዋርደዋል። አሕዛብ የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል ባይኖራቸውም በልባቸው ውስጥ የእግዚአብሔር ቃል ተጽፎላቸዋል (ሮሜ 2፡14–15)። ወይም ደግሞ የእግዚአብሔርን እውነት ከተፈጥሮ ተመልክተዋል [መዝ. (19)፡1–6፤ ሮሜ 1፡18–21]። እነርሱም ቢሆኑ በዓመፃቸው ምክንያት ስለ እግዚአብሔር የሚያስቡበትን ዓቅም አጥተዋል። በሰዎች እጅ የተሠሩትን አማልክት ማምለካቸው ምን ያህል ሞኝነት እንደሆነ ለመረዳት አልቻሉም። አንድ ሰው ጣዖታትን ወይም ማናቸውንም ዓይነት የሐሰት ሃይማኖቶች በሚያመልክበት ጊዜ ለመንፈሳዊ ዕውርነት መዳረጉ ሳያንስ ከጣዖቱ በስተጀርባ ያለው ሰይጣን ሕይወቱን በመቆጣጠር የተግባራቱን ጅልነት እንዳይገነዘብ ያደርጋል።

<u>ሁለተኛ</u>፥ ምንም እንኳ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ ባይጠቀስም ከእነዚህ አማልክትና ጣዖታት በስተጀርባ ሰይጣን በመሥራት ላይ መሆኑ በ1ኛ

ቆሮንቶስ 10፡18–22 ተገልጾአል። ሰይጣን ሰዎች እንደ ዛፎች፥ ወንዞች፥ ወዘተ... ያሉ ጣዖታት አማልክት እንደሆኑ እንዲያምኑለት የማያደርገው ጥረት የለም። እንዲሁም ደግሞ ሰዎች የሐሰት ትምህርቶችን እንዲከተሉ ለማድረግ ተግቶ ይሠራል። በዚህም እርሱን ወደ ማምለኩ ደረጃ ይደርሱና ኢየሱስ ክርስቶስ በሙታንና በሕያዋን ላይ ለመፍረድ ሲመጣ በሰይጣን ላይ የሚያወርደውን ፍርድ ይጋራሉ።

16ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ሰዎች በአሳብ ደረጃ ሞኝነት ያመዘነበት እንዲህ ዓይነት መንፈሳዊ ዕውርነት ሲያራምዱ ያየኸው እንዴት ነው? ለ) ይህ ስለ ሰይጣን የማሳሳት ችሎታ ምን ያስተምረናል? ሐ) ይህ ከሰዎች የምንሰማቸውንና የምንማራቸውን ነገሮች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር እንድናነጻጽር የሚያስጠነቅቀን እንዴት ነው?

ሐ. ለእግዚአብሔር ሕዝብ ማስገንዘቢያ (ኢሳ. 44፡21–23 አንብብ)

በስደት ወይም በኢየሱስ ክርስቶስ በማያምኑ ሰዎች መካከል ያለ ሰው በቀላሉ አስፈላጊ ነገሮችን ሊዘነጋ ይችላል። ብዙውን ጊዜ ዓለም የሚያስተምረውን ነገር በማመን እንስታለን። ጥሩ ክርስቲያናዊ ወዳጆች በሌሉበት አካባቢ ስንኖር አስተሳሰባችንን ለማጥራት በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ ረዥም ጊዜ ማሳለፍ የሚኖርብን ለዚህ ነው። እግዚአብሔር አይሁዶች በምርኮ በነበሩበት ጊዜ አያሌ ነገሮችን እንዲያስታውሱ ነግሮአቸዋል።

1. ባሪያዎቹ እንደመሆናቸው ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ልዩ ግንኙነት ማስታወስ ነበረባቸው። እግዚአብሔር ፈጥሮአቸዋል። አሕዛብ የሚያመልኩባቸውን ጣዖታት የሠሩ ሲሆኑ፥ እግዚአብሔር ግን የሚያመልኩትን ሕዝብ ፈጥሮአል።

2. ከእግዚአብሔር ጋር ካላቸው ልዩ ግንኙነት ሳቢያ አይረሳቸውም። ለኃጢአታቸው በከፍተኛ ደረጃ ቢቀጣቸውም አልተዋቸውም ነበር።

3. እግዚአብሔር ኃጢአታቸውን ሁሉ ረስቶ አይሁዶችን ወደ በረከት ስፍራቸው የሚመልስበት ዘመን ይመጣል። በዚያን ጊዜ ኃጢአታቸው ጠዋት ታይቶ ፀሐይ ስትወጣ እንደሚወገድ ጤዛ ከመታሰቢያነት ይርቃል።

4. ሙሉ መቤዠት የሚመጣበትን የወደፊት ጊዜ በተስፋ መጠባበቅ ነበረባቸው። ወደ እርሱ ከተመለሱ እርሱም ወደ እነርሱ በመመለስ በምድር ላይ ቆይታቸው ጊዜያዊና ከፊል በረከት እንዲያገኙ ያደርጋል። አንድ ቀን ግን የእግዚአብሔርን ሙሉ ክብር ወደሚያዩበት ሙሉ የቤዛነት ዘመን ይደርሳሉ። በዚያን ዕለት ፍጥረት ሁሉ ከኃጢአት ርቆ በደስታ ይሞላል። ይህ ሰዎች እንደ ዛፎች፥ ፀሐይ፥

ጨረቃ፥ ከዋክብት የመሳሰሉትን የተፈጥሮ አካላት ከሚያመልኩበት የሚጻረር ነው። ቅዱስ ጳውሎስ እንዳለው ፍጥረት የእግዚአብሔርን ልጆች መገለጥ በናፍቆት በመጠባበቅ ላይ ይገኛል (ሮሜ 8፡18–22)።

17ኛ ጥያቄ፡– እነዚህን ነገሮች በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ላይ በምንሆንበትም ጊዜ ማስታወስ የሚኖርብን ለምንድን ነው?

3. ኢየሩሳሌም እንደገና የአይሁዶች መኖሪያ ትሆናለች (ኢሳ. 44፡24–28 አንብብ)

በኢሳይያስም ሆነ በእኛ ዘመን እውነተኛ ነቢያት እንዳሉ ሁሉ ሐሰኞችም አሉ። ኢሳይያስ ወደፊት የሚፈጸሙትን ክስተቶች በትክክል ሊተነብይ ሲችል፥ በአይሁድ መካከል ሌላ መልእክት የሚያስተላልፉ ሰዎች ነበሩ። በዚህ ጊዜ ማን እውነተኛ ማን ሐሰተኛ እንደሆነ መለየቱ አስቸጋሪ ነበር። ነገር ግን በትንቢቱ ተፈጻሚነት እግዚአብሔር ኢሳይያስ እውነተኛ ነቢዩ እንደሆነ ያሳይ ነበር።

እግዚአብሔር ከጻድቅ ሕዝቡ ጋር ባለው ግንኙነት (*ከማጎፀን ሰለሠራቸው*) እና በእግዚአብሔር ኃይል ምክንያት (ሁሉን ስለፈጠረ፥ ሰማያትን ለብቻው ስለዘረጋ፥ ምድርንም ስላጸና) አይሁዶቹ የእግዚአብሔር ትንቢት በትክክል እንደሚፈጸም እርግጠኞች መሆን ነበረባቸው። እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን ለመፈጸም ሲሠራ ሁለት ነገሮች ተግባራዊ ይሆናሉ። <u>በመጀመሪያ</u>፥ የተሳሳቱ ሰዎች ይገለጣሉ። በዚያን ጊዜ ሐሰተኛ አስተማሪዎች፥ ነቢያትና ምዋርተኞች ተጋልጠው ከእግዚአብሔር ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት እንደሌላቸው ይረጋገጣል። እነዚህ ሐሰተኛ ነቢያትና አዋቂዎች ኢየሩሳሌም እንደማትደመሰስ በመግለጽ ሕዝቡ ከዓለም ጋር ስምምነት በማድረግ ከእምነቱ ወደ ኋላ እንዲመለስ ያበረታቱ ነበር። አንድ ቀን ግን ዕቅዳቸው ሁሉ ውድቅ ሆኖ ይዋረዳሉ። በሰብአዊ እውቀት ላይ የተመሠረቱና አዋቂዎች ነን ብለው ያሰቡት ፈሪሃ እግዚአብሔር የሌለባቸው ሰዎችም ይዋረዳሉ።

<u>ሁለተኛ</u>፥ እንደ ፈቃዱ ዓላማ ሁሉን የሚሠራው አምላክ የማይቻለውን ያደርጋል። ፍርዱን ያመጣባትን ከተማ ይነበዮታል። አይሁዶች ወደ ምርኮ በተወሰዱ ጊዜ ባዶአቸውን የቀሩት የይሁዳና የኢየሩሳሌም ከተሞች እግዚአብሔር አይሁዶችን ከምርኮ ሲመልስ እንደገና ታድሰው በሕዝብ ይሞላሉ። ከተስፋዱቱ ምድር ሲመለሱ ከግብፅ በወጡበት ጊዜ ቀይ ባሕርን ባደረቀበት መንገድ የሚያጋጥሟቸውን መሰናክሎች ሁሉ ያስወግድላቸዋል።

እግዚአብሔር ሥራውን ለማከናወን ቂሮስ የተባለ ሰው እንደሚጠቀም ገልጾአል። የዚህ የሰሜናዊ ተዋጊ ስም ለመጀመሪያ ጊዜ

የተነገረን በዚህ ስፍራ ነው። ቂሮስ ከኢሳይያስ ዘመን ከ150 ዓመታት በኋላ ተነሥቶ የተባበሩት የሜዶንና የፋርስ ንጉሥ በመሆን ባቢሎንን ያሸነፈ ሰው ነው። እግዚአብሔር ቂሮስን «እረኛዬ» ሲል ፈቃዱን ለመፈጸም ከሚነሡት ነገሥታት ጋር አመሳስሎታል (2ኛ ሳሙ. 5፡2፤ ኤር. 23፡2)። የእረኞች አለቃ የሆነው እግዚአብሔር የተበታተኑትን እስራኤላውያን ሰብስቦ ወደ አገራቸው ለመምራት ቂሮስን በእረኛነት ለመጠቀም ፈለገ። ቂሮስ እግዚአብሔርን በግል ባያውቀውም ሕዝቡን ከምርኮ እንዲመልስ የተሰጠውን ዓላማ ፈጽሞታል። ስለሆነም ሳያውቅ የእግዚአብሔር ሕዝብ እረኛ ሆኖአል። በእርሱ አማካኝነት የኢየሩሳሌም ከተማና ቤተ መቅደስ ዳግም ይሠራ ነበር። ይህም ቂሮስ ባቢሎንን ካሸነፈ በኋላ አይሁዶች ወደ አገራቸው ተመልሰው ቤተ መቅደሳቸውንና ከተማቸውን እንዲሠሩ በፈቀደበት ወቅት ተፈጻሚነትን አግኝቷል (ዕዝራ 1፡2–4፤ 6፡3–5)።

18ኛ ጥያቄ፡– እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሠራ ከዚህ ምዕራፍ ምን እንማራለን?

ሦስተኛ ቀን ኢሳይያስ 45

በለጠና ተመስገን በአንድ ኳየር ውስጥ ያገለገሉ፥ በአንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ቤት የተማሩና በአንድ ወቅት ያገቡ የቅርብ ጓደኛሞች ነበሩ። ጊዜው እየገፋ ሲሄድ ግን በሕይወታቸው ውስጥ ነገሮች የተለየ ገጽታ ይይዙ ጀመር። በለጠ ጥሩ ሥራ ከማግኘቱም በላይ ሚስቱ መጀመሪያ ቆንጆ ሴት ልጅ፥ ከዚያም ወንድ ልጅ ወለደችለት። በጥሩ ሥራው ማራኪነት የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌ ሆኖ ተመረጠ። ተመስገን ግን ብዙ ቢፍጨረጨርም ቋሚ ሥራ ሊያገኝ አልቻለም። የወለደው ልጅም የአእምሮ ዘግምተኛ ሆነ። ሁለተኛ ልጁ ደግሞ በዓመቱ ሞተበት። ብዙ ገንዘብ ስላልነበረው ለቤተ ክርስቲያን ሽምግልና አልተመረጠም። ወዲያውም መራራ ጥያቄዎች ወደ አእምሮው ይጎርፉ ጀመር። እግዚአብሔር ለምን ይህን አደረገ? ምን ኃጢአት ሠርቻለሁ? ጓደኛዬን እየባረከ እኔን የረገመኝ ለምንድን ነው?

19ኛ ጥያቄ፡– ሀ) አንተ በተመስገን ቦታ ብትሆን ስለ እግዚአብሔር የምታነሣቸው ጥያቄዎችና ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖርህ ግንኙነት ምን ሊመስል እንደሚችል ተናገር። ለ) የበለጠና የተመስገን ጓደኝነት እንዴት የሚሆን ይመስልሃል? ለተመስገን በበለጠም ላይ ማማረር ለምን የሚቀልለው ይመስልሃል? ሐ) ክርስቲያኖች በተመስገን ዓይነት ትግል ውስጥ ሲፍጨረጨሩ ያየህባቸውን አጋጣሚዎች ግለጽ። መ) የቤተ ክርስቲያኒቱ መሪ ብትሆን ተመስገንን ለማጽናናት የምትሞክረው እንዴት ነበር? ሠ) ኢሳይያስ 45፡7፥ 9–10፥15 አንብብና በዚህ ስፍራ ተመስገን ልብ ሊላቸው የሚገባቸው

እውነቶች የትኞቹ እንደሆኑ ግለጽ። ተመስገንን ሊረዳ የሚችል ሌላ ጥቅስ የትኛው ነው?

አንዳንድ ሰዎች እየተሳካላቸው ሌሎች በከፍተኛ ችግሮች ለምን እንደሚናጡ ማብራሩቱ አስቸጋሪ ነው። ምንም እንኳ ክርስቲያኖች ለዚህ ምክንያቱ ከሰዎች ጽድቅ ጋር የተያያዘ መሆኑን ወደ ማመኑ ቢያዘነብሉም ይህ ግን ሁልጊዜም እውነት አይደለም። በምድር ላይ በብዙ ኃጢአት የሚቆሽሹ ሰዎች ከችግሮች እያመለጡ በእግዚአብሔር የሚታመኑ ሰዎች በከፍተኛ ደረጃ ሲታገሉ እንመለከታለን [መዝ. (10)፤ (37)፡35–36፤ (73)]። ስለሆነም የሰዎችን መንፈሳዊነት ከሚጋፈጡት ሁኔታ አንጻር ከመፍረድ ልንታቀብ ይገባል። በሌላ በኩል፥ ራሳችን ፍትሐዊነት የጎደለው በሚመስል ሁኔታ ውስጥ ካለን ወደ ሌሎች ሰዎች ተመልከተን እንዳናማርርባቸው ልንጠነቀቅ ይገባል። የሚደርስባቸው ሁኔታ በእነርሱ ውሳኔ የመጣ አይደለም። ለአንተም ሆነ ለእነርሱ የሚደርሰውን የሚወስነው እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ለኢሳይያስ እንደተናገረው፥ ለአንዱ ሰው ወይም አገር መርገምን፥ ለሌላው ደግሞ በረከትን የሚመርጠው እርሱ ነው። የተፈጠረው ሰው ፈጣሪውን ስለ መንገዶቹ ሊገዳደረው አይችልም። ኢሳይያስ የሚሳየን ግን የዘላለሙ መንግሥት እስኪመጣ ድረስ ሁኔታው እንደሚቀጥል ነው። የእግዚአብሔር ልጆች ሊያውቁ የሚገባቸው ቢኖር በመንግሥተ ሰማይ ሁሉ ነገር መልካም እንደሚሆን እግዚአብሔር እንባዎቻቸውን እንደሚያብስና ሕመም እንደማይኖር ነው። ከእግዚአብሔር ዘንድ የሚመጣውን የሙሉ በረከት ጊዜ እየተጠባበቅን ሳለ እግዚአብሔር በመከራ አማካኝነት ሊያስተምረን የሚፈልገውን ነገር መማራችንን መቀጠል አለብን።

20ኛ ጥያቄ፡– ኢሳይያስ 45ን አንብብ። (ሀ) ቂሮስ የተገለጸው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ከእርሱ ጋር የነበረው ግንኙነት ምን እንደሆነና እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግለት ግለጽ። እግዚአብሔር ይህንን ለቂሮስ ለምን እንደሚያደርግ የተገለጹትን የተለያዩ ምክንያቶች ዘርዝር። (ለ) በምድር ላይ የሚዘንቡ ሁለት ነገሮች ምንድን ናቸው? ይህ ምንን የሚያመለክት ይመስልሃል? (ሐ) ሰዎች ማስጠንቀቂያ የተሰጣቸው በፈጣሪያቸው ላይ ምን ዓይነት አመለካከት እንዳይኖራቸው ነው? (መ) እግዚአብሔር በመለኮታዊ ምርጫው ለሕዝቡ ምን እንደሚያደርግ ተናገረ? (ቁ. 11–13)። (ሠ) እግዚአብሔር ሕዝቡን ከመባረኩ የተነሣ ግብፃውያን፥ ኢትዮጵያውያንና ሳባውያን ምን ያደርጋሉ? እግዚአብሔር በታሪክ ሲሠራ አይተው የተማሩት ነገር ምንድን ነው? (ቁ. 14)። (ረ) በጣዖታትና በአምላኪዎቻቸው ላይ የሚደርሰው ምንድን ነው? በእንጻሩ በእስራኤል ላይ የሚሆነው ምንድን ነው? (ሰ) እግዚአብሔር በዓለም ላይ ታላቅነቱን ያረጋገጠው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ለዓለም ሕዝብ ስለ ራሱ ያስተማረው ምንድን ነው? ለዓለም

ሕዝብ የሰጠው ትእዛዝ ምንድን ነው? (ሸ) እግዚአብሔር ሥራውን በሚያጠናቅቅ ጊዜ የታሪክ ፍጻሜ ምን ይሆናል? (ቁ. 23)። ሰዎች በዚያን ጊዜ ምን ይረዳሉ? (ቁ. 24)። (ቀ) ለእግዚአብሔር የመኖርንና ያለመኖርን ጠቀሜታ የመጨረሻው ዘመን የሚለየው እንዴት ነው?

1. እግዚአብሔር ቂሮስን እንደተቀባ መሣሪያው አድርጎ መረጠ (ኢሳ. 45፡1–7)

ሀ. እግዚአብሔር ስለ ቂሮስ የሰጠው ገለጻ (ኢሳ. 45፡1–3)

እግዚአብሔር ከ150 ዓመታት በኋላ ለሚነሣው ንጉሥ በኢሳይያስ አማካኝነት መልእክት አስተላለፈ። እግዚአብሔር ከቂሮስ ጋር ያለውን ግንኙነት የገለጸው በሚከተለው መንገድ ነበር።

1. እግዚአብሔር ቂሮስን ይቀባዋል። በዕብራይስጥ ይህ ቃል «መሢሕ» ሲሆን፥ በግሪክ «ክርስቶስ» ነው። ይህም በአዲስ ኪዳን ለኢየሱስ ክርስቶስ የተሰጠ ስም ነው። ይህ ስያሜ የመጣው በብሉይ ኪዳን እግዚአብሔር ሕዝቡን የሚመራ ንጉሥ ለመሪነት ከሚመርጥበት ልምምድ ነው (ለምሳሌ፥ ዳዊት [1ኛ ሳሙ. 16])። እግዚአብሔር አይሁዶችን ከምርኮ ያስለቀቅ ዘንድ አማኝ ያልሆነውን አሕዛብ ለንጉሥነት መረጠ።

2. እግዚአብሔር የቂሮስን ቀኝ እጅ ይይዛል። ቀኝ እጅን መያዝ የጥበቃና የምሪት ተምሳሌት ሲሆን፥ እግዚአብሔር ቂሮስ ዓላማውን ከዳር ያደርስለት ዘንድ ይህንኑ ተግባር ይፈጽማል። በተጨማሪም ይህ በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር መሆንን ያመለክታል። ያነሣውና ዕቅዱን ሳይፈጽም እንዳይቀር እጁን የሚይዘው እግዚአብሔር ነበር። ቂሮስ ነገሩን ባያውቀውም የራሱን ሳይሆን እግዚአብሔር የወጠነውን ዕቅድ ይፈጽማል።

3. ቂሮስ አሕዛብን ይገዛል፤ የነገሥታትን ወገብ ይፈታል። ምናልባትም ቂሮስ ባቢሎንን፥ የትንሹ እስያን አገሮች፥ የመካከለኛውን ምሥራቅ ሁሉ እስከ ግብፅ ድረስ (ከመጽሐፉ በስተጀርባ የሚገኘውን ካርታ ተመልከት) ለማሸነፍ የቻለው በራሱ ችሎታና በሠራዊቱ ብርታት እንደሆነ ሊያስብ ይችላል። እግዚአብሔር ግን የኃይሉ ምንጭ እንደሆነ በመግለጽ፥ አሕዛብን እንዲያሸንፍና ነገሥታትን እንዲማርክ እንደሚረዳው ተናግሮአል።

4. እግዚአብሔር በሮችን ይከፍትለታል። በጥንት ዘመን በከተሞች ዙሪያ ትላልቅ ቅጥሮች ይሠሩ ነበር። የጠላት ሠራዊት በሚመጣበት ጊዜ ከመቅጽበት የሚዘጉ በሮችም ነበሯቸው። አንዳንድ የባቢሎን በሮች ከነሐስ የተሠሩ ጠንካሮች ቢሆኑም፥ እግዚአብሔር ለቂሮስ

በማገዝ ይከፍታቸዋል። እንዳይዘጉም ያደርጋል። ስለሆነም ቂሮስ የማይዘለቁ ይመስሉ የነበሩትን ከተሞች በቀላሉ ይወራቸዋል። በራእይ 3፡7 ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተጠቀሰው አሳብ የመጣው ከዚህ አሳብ ይመስላል።

5. ተራሮች ሁሉ ሜዳ ስለሚሆኑለት የቂሮስ መንገድ ለማሸነፍ የቀለለ ይሆናል። (ማስታወሻ፡ ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር ለቂሮስ በቀጥታ ይናገራል።) እነዚህ ተራሮች በሰው መንገድ ላይ የሚገኙትን የተለያዩ መሰናክሎች እንደሚያሳዩ ተመልክተናል። እግዚአብሔር ሕዝቡ ወደ አገራቸው የሚያደርጉትን ጉዞ ለማቃለል ተራሮችን ሁሉ ከፊታቸው እንደሚያስወግድ ገልጾአል (ኢሳ. 42፡15–16 ተመልከት)። አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ከቂሮስ ፊት ተራሮችን ትክክል በማድረግ የእግዚአብሔርን ዕቅድ በቀላሉ የሚፈጽምበትን ሁኔታ እንደሚያመቻች ተመልክቷል። ቂሮስ ያሸነፈው በራሱ ጥበብና ችሎታ፥ ሠራዊትና ብቃት ሳይሆን በእግዚአብሔር ዝግጅትና ማስቻል ነበር።

6. እግዚአብሔር የወረራቸውን አገሮችና ከተሞች ሀብት ለቂሮስ ይሰጠዋል። ከእግዚአብሔር እይታ አንጻር፥ እነዚህ አገሮች ቂሮስና ሠራዊቱ በውጊያው ወቅት ያገኙአቸው ሳይሆኑ የእግዚአብሔርን ዓላማዎች በመፈጸማቸው የተሰጣቸው ሽልማት ነው።

ለ. እግዚአብሔር በቂሮስ አማካኝነት ለመሥራት የመረጠባቸው ሦስት ምክንያቶች (ኢሳ. 45፡3–7 አንብብ)

እግዚአብሔር ቂሮስን የመረጠው ታላቅና የሚገባው ሰው በመሆኑ ሳይሆን ለራሱ ዓላማዎች ሲል ነው።

1. ቂሮስ ራሱ በተለየ ሁኔታ በእግዚአብሔር እንደተመረጠና የሚያሸንፍበትን ኃይል እንዳገኘ ያውቅ ዘንድ እግዚአብሔር ቂሮስን በመጥራት የዓለምን አገሮች ሰጠው። እግዚአብሔር ቂሮስን በስሙ እንደጠራው ገልጾአል። ይህም እግዚአብሔር የቂሮስን ሕይወትና አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ እንደሚቆጣጠር የሚያመለክት ነው። ቂሮስ እግዚአብሔርን ያከብር ዘንድ የእግዚአብሔር እጅ ሲሠራ የማየት ዕድል አግኝቷል። ከዕዝራ 6፡7 እና 7፡27 እንደምናነበው በተወሰነ ደረጃ ቂሮስ ይህንን ያውቅ ነበር። ከሌሎች ምንጮች እንደሚታየው ግን አሁንም ቢሆን ቂሮስ የባቢሎናውያንን አማልክት የሚያመልክና ወደ ደኅንነት ያልመጣ ሰው ነበር። ባቢሎንን ባሸነፈ ጊዜ አይሁዶች በትንቢተ ኢሳይያስ ስለ እርሱ የተነገሩትን የተለያዩ ትንቢቶች ሲያሳዩት አምኖ እንደለቀቃቸው ታሪክ ጸሐፊው ጆሲፈስ ገልጾአል። ምሑራን የዚህን ታሪክ እውነተኛነት ለማረጋገጥ ባይችሉም፥ ቂሮስ ባቢሎንን

ሲያሸንፍና አይሁዶችን ወደ አገራቸው ሲያስናብት የእግዚአብሔርን ሚና እንደተገነዘበ መጽሐፈ ዕዝራ በግልጽ ይናገራል።

እግዚአብሔር ለሕዝቡ የተለያዩ ስጦታዎችን ከሚሰጥባቸውና በእነርሱም አማካኝነት ከሚሠራባቸው ምክንያቶች አንዱ ሕዝቡ እየተጠቀመባቸው እንደሆነ እንዲያውቁ ነው። እግዚአብሔር ለአንዳንዶች የመዝሙርን ስጦታ የሚሰጠው ያንን ስጦታ ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደተቀበሉ አውቀው በዝማሬ እንዲያመሰግኑት ነው። የማስተማር፥ የመስበክና ወንጌልን የማሰራጨት ስጦታዎችም ሁሉ በዚህ መልኩ የሚከናወኑ ናቸው። የሚያሳዝነው ግን አንዳንድ ሰዎች ይህንን ስጦታ የተቀበሉት እነርሱ የተለዩ ሰዎች በመሆናቸው ምክንያት እንደሆነ ስለሚያስቡ በትሕትና በማገልገል ፋንታ ይታበያሉ።

21ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በሆነ መንገድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስጦታ እንደተቀበሉ የምታውቃቸውን አንዳንድ ሰዎች ስም ዘርዝር። ለ) እነዚህ ሰዎች ይህንን ስጦታ የሰጣቸው እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ማሰብ የሚያስፈልጋቸው ለምንድን ነው? ሐ) ምን ያህል መልካም ተውህቦ ያላቸው ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ፊት ትሑታን ሆነው እንደመኖር በትዕቢት እንደተያዙ ግለጽ። ይህ የሆነው ለምንድን ነው?

2. እግዚአብሔር ቂሮስን የመረጠውና የረዳው ስለ ባሪያው ያዕቆብ፥ ስለ መረጠውም ስለ እስራኤል ሲል ነው። እግዚአብሔር ለቂሮስ የወረራ ብቃት የሰጠበት ሁለተኛው ምክንያት ለተመረጠው ሕዝቡ ለአይሁዶች ዓላማ ስላለው ነበር። እግዚአብሔር ቂሮስን በመሣሪያነት በመጠቀም ሕዝቡን ከባቢሎን ምርኮ ወደ አገራቸው ይሁዳ ሊመልሳቸው ፈለገ። ቂሮስ የእግዚአብሔርን ሕዝቦች ይጠቀም ዘንድ በእግዚአብሔር እጅ የሚገኝ ያልታወቀ መሣሪያ ነበር። እግዚአብሔር ቂሮስን በቁልምጫ ስም ጠርቶታል። እግዚአብሔር ለዓላማው ሲል የዓለም ታላቅ ንጉሥና ገዥ አድርጎታል። በዚህ ሁሉ መሀል ቂሮስ እግዚአብሔር እየተጠቀመበት መሆኑን አያውቅም ነበር። ስለዚህም «አንተ ግን አላወቅኸኝም» ብሎታል።

22ኛ ጥያቄ፡– ሀ) እግዚአብሔር ክርስቲያን ያልሆነውን ሰው ሳያውቅና ሳይፈቅድ ለራሱ ዓላማ ሲጠቀም ያየህበት ሁኔታ ካለ ግለጽ። ለ) ይህ ስለ እግዚአብሔር ኃይል ምን ያስተምረናል?

3. እግዚአብሔር ቂሮስን የመረጠበትና ኃይልን ያስታጠቀበት የላቀ ዓላማ ነበር። ይህም ለቂሮስ ወይም ለእስራኤል በማሰብ ሳይሆን እግዚአብሔር ከምድር ሁሉ ክብርን ለራሱ ሊቀበል ስለፈለገ ነው። በፀሐይ መውጫ (በምሥራቅ) እና በመጥለቂያው (በምዕራብ) የሚገኙ አገሮች ሁሉ እርሱ ብቻ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ አውቀው

እንዲያመልኩት ይሻል። እግዚአብሔር እነርሱ የፈጠሯቸው የግል አማልክት ከንቱዎች እንደሆኑ ሕዝቦች ሁሉ እንዲገነዘቡ ይፈልጋል። ከ150 ዓመታት በፊት ቂሮስ በዓለም ላይ እንደሚነግሥ የተነበየ አንድ እውነተኛ አምላክ ብቻ ነበር። አይሁዶች አምልኮተ ጣዖታቸውን እርግፍ አድርገው ትተው ብቸኛውን እውነተኛ አምላክ ሊያመልኩት ይገባ ነበር። በመጨረሻም፥ በእስራኤላውያን ከምርኮ መመለስ፥ በመሢሕ የኋላ ኋላ ምጽአትና በወንጌሉ ስርጭት በዓለም ሁሉ ሰዎች ዛሬ የእስራኤል አምላክ እውነተኛ አምላክ እንደሆነ በመገንዘብ ላይ ናቸው።

23ኛ ጥያቄ፡– ሀ) ይህ በዓለም የእግዚአብሔር ዋና ዓላማ የሆነው እንዴት ነው? ለ) ይህንኑ ዓላማ ለመፈጸም ዛሬ እግዚአብሔር ማንን ጠራ? (ማቴ. 28፡19–20 ተመልከት)።

ዘላለማዊና ሁሉን ቻይ አምላክ እንደመሆኑ እግዚአብሔር በዚህች ዓለም የሚፈጸሙትን ነገሮች ሁሉ በፍጹማዊነት ይቆጣጠራል። ብርሃንን (ሰላም፥ ብልጽግና፥ በረከት) እና ጨለማን (አደጋ) የሚያመጣው እርሱ ነው። (ማስታወሻ፡ የአማርኛው መጽሐፍ ቅዱስ «አደጋ» የሚለውን ቃል «ክፋት» ሲል ተርጉሞታል። ይህ ሥነ ምግባራዊ ብልሽትን የማያመለክት መሆኑን መገንዘቡ ተገቢ ነው። እግዚአብሔር ሥነ ምግባራዊ ክፋትን አይፈጽምምና። ነገር ግን እግዚአብሔር በሰው ልጆች ላይ እንደ ጦርነት፥ ረሃብ፥ የምድር መንቀጥቀጥ የመሳሰሉትን የተፈጥሮ አደጋዎች ለማምጣት እንደሚችል በሚያሳይ መልኩ «አደጋ» የሚለውን ቃል መጠቀሙ መልካም ነው።) አይሁዶች ኃጢአትን በመሥራታቸው እግዚአብሔር የምርኮን ጽልመት በመስጠት ለባቢሎናውያን ደግሞ ምርኮ የመበዝበዝን ብርሃን አመጣ። አሁን ደግሞ አይሁዶች የበረከትን ብርሃን ያገኙ ዘንድ ለቂሮስ የድል ነሺነትን ብርሃን፥ ለባቢሎናውያን ደግሞ የሽንፈትን ጽልመት ያጎናጽፋቸዋል። እግዚአብሔር ክስተቶችን ሁሉ በሉዓላዊነት ይቆጣጠራል።

ለክርስቲያኖች ይህንን ማስታወሱ ጠቃሚ ነው። እግዚአብሔር ለሕዝቡ በረከትን ብቻ እንደሚሰጥና እንደ ድህነት፥ በሽታ፥ ወይም ሞት የመሳሰሉት አደጋዎች እንደማይደርሱባቸው የሚያስተምሩ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን አሉ። እግዚአብሔር ግን በሉዓላዊነቱ በሕዝቡ ላይ አደጋን የሚያመጣባቸው ጊዜያት አሉ። በረከትም ሆነ መከራ የሚመጣው በእግዚአብሔር ፈቃድና ሉዓላዊ ቁጥጥር ነው። እነዚህ የመከራ ጊዜያት የሚመጡት ሁልጊዜም ለእኛ፥ ለሕዝባችን፥ ለቤተ ክርስቲያንና ለዓለም በሚጠቅም መልኩ ነው። ዓላማውን ላንመለከት

ብንችልም፥ እግዚአብሔር ነገሮችን በመቆጣጠር የኋላ ኋላ እርሱን ለሚወዱት ወደ መልካምነት እንደሚለውጥ እናውቃለን (ሮሜ 8፡28)።

24ኛ ጥያቄ፡– ይህ እውነት መከራ ለሚጋፈጡትም ሆነ በእግዚአብሔር በረከት ውስጥ ለሚኖሩት ክርስቲያኖች አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው?

2. እግዚአብሔር ለዓለም ሁሉ ጽድቅንና ደኅንነትን ያመጣል (ኢሳ. 45፡8 አንብብ)

በዚህ ምንባብ ውስጥ የተናጋሪው ማንነት አልተጠቀሰም። ሰማያትና ምድር ጽድቅንና ደኅንነትን ወደ ምድር እንዲልኩ በተምሳሌታዊ አገላለጽ የሚያዛቸው እግዚአብሔር ይሆን? ወይስ ይህ ኢሳይያስ እግዚአብሔር በምድር ላይ የጽድቅን ዘመን እንዲያዘንብ የጠየቀበት ጸሎት ነው? ሁለቱም የሚያስኬዱ አማራጮች ናቸው። ትእዛዙ የተሰጠው ዝናብ ከሰማይ ወደ ምድር እንደሚወርድ ሁሉ ጽድቅም ከሰማይ (ከእግዚአብሔር) በምድር ላይ እንዲዘንብ ነው። በፍጥረት መጀመሪያ ጉም ከምድር ወጥቶ መሬትን እንዳጠጣ (ዘፍጥ. 2፡6)፥ እንዲሁ ደኅንነት ምድርን እንዲያጠጣት ታዘዘ። ደኅንነትና ጽድቅ በአንድነት አድገው ምድርን ይሸፍናሉ። የዝናብን ምስያ ከሰማይ፥ የምንጭን ደግሞ ከምድር በመጠቀም እግዚአብሔር የመጨረሻው ዘመን ባሕርይ አንድ እንደሚሆን ገልጾአል። ይኸውም ለእግዚአብሔር ሕዝብ ሁሉ ጽድቅ የሚገኝበትና ሰዎችም ከሚያስፈራቸው ነገር ሁሉ የሚድኑበት በመሆኑ ነው። ይህ በቂሮስ በከፊል ተፈጻሚነት አግኝቷል። እግዚአብሔር በቂሮስ አማካኝነት አይሁዳውያንን ከባቢሎናውያን ምርኮ በማስለቀቅ ነገሮችን በመጠኑ ያሻሽልላቸው ነበር። ቂሮስ ወደ አገራቸው እንዲሄዱ እንዲፈቅድ በማድረግ ለአይሁዶች ደኅንነትን ያመጣላቸው ነበር።

ዳሩ ግን ይህ ትንቢት ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የሚነግሥበትን የመጨረሻውን ዘመን እንደሚያመለክት አያጠራጥርም። ዘላቂ ጽድቅና ደኅንነት ምድርን የሚሞላው ያን ጊዜ ብቻ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በመንገሡ ምክንያት በምድር ሁሉ ፍትሕና እኩልነት ይሰፍናል።

3. ከእግዚአብሔር ጋር መከራከር ትክክል የማይሆነው ለምንድን ነው? (ኢሳ. 45፡9–10 አንብብ)

እግዚአብሔር በእያንዳንዳችን ውስጥ ትክክልና ፍትሐዊ ስለሆነውና ስላልሆነው የምናውቅበትን የሕሊና ዳኝነት አስቀምጦአል። ስለሆነም በጥሩ ሰዎች ላይ ክፉ ነገሮች ሲደርሱ የፍትሐዊነት ጥያቄ ይተናነቀናል። ጥሩ ሰዎች በሕመምና በሞት ሲሠቃዩ፥ አገራችን

በጦርነት ስትታመስ «ለምን?» ብለን እግዚአብሔርን ለመጠየቅ እንፈልጋለን። ይህ ስሕተት እንደሆነ በመግለጽ ከእግዚአብሔር ጋር ልንከራከር እንሻለን። አይሁዶች ወደ ባቢሎን በምርኮኛነት በተወሰዱ ጊዜ እንዲህ ዓይነት አመለካከት እንደነበራቸው አይጠረጠርም። «እግዚአብሔር ከእኛ በላይ እጅግ በከፉት ባቢሎናውያን እንዴት ይቀጣናል? ፍትሐዊ አይደለም» ማለታቸው አይቀርም። ወይም ደግሞ እግዚአብሔር ኃያልና አስፈሪ በሆነው አረማዊ ንጉሥ አማካኝነት ነፃ ሊያወጣቸው መፈለጉን አይደግፉም ይሆናል።

ምንም እንኳ እግዚአብሔር በትሕትና እንድንጠይቀው የሚፈቅድና አንዳንድ ጊዜ መልሶችን የሚሰጠን መሆኑ ቢታወቅም፥ የሚፈልገውን የማድረግ ሉዓላዊ መብቱን የሚቀናቀን ጥያቄ እንድናነሣበት አይፈቅድም። እንዲህ ዓይነት ጥያቄዎችን ማንሣቱ የእግዚአብሔርን የፈጣሪነትና የሁሉን ቻይነት፥ የእኛንም የተፈጣሪነት ሚና መዘንጋት ነው። ኢሳይያስ እግዚአብሔር በእኛ ላይ እንዲደርሱ የሚመርጣቸውን ነገሮች የመጠየቅ መብት እንደሌለን ለማሳየት ሁለት ማብራሪያዎችን ተጠቅሟል። <u>መጀመሪያ</u>፥ ስለ ሸክላና የሸክላ ሠሪ የቀረበ ማብራሪያ አለ። ሸክላ የሸክላ ሠሪውን፥ «ምጣድ ልታደርገኝ ሲገባ ለምን እንስራ አደረግኸኝ?» ብሎ እንደማይሟገት ሁሉ፥ እኛም የእግዚአብሔርን መንገዶች የመጠየቅ መብት የለንም። አንድ የተፈጠረ ነገር የፈጠረው ነገር እጆች ወይም ኃይል እንደሌለው የማጉተምተም መብት የለውም። ሠሪው በእጆቹ ተጠቅሞ ስለፈጠረው እንዲህ ዓይነቱ ጥያቄ መሠረት የሌለው ነው። ለእኛም እግዚአብሔር እንደማያውቅ ማሰቡ የፈጣሪንና የተፈጣሪን ቅደም ተከተል ከማዛባቱ ባሻገር እግዚአብሔርን ደካማና መልካም ነገር ለመፍጠር የማይችል ያስመስለዋል። ከእግዚአብሔር ታላቅነት ጋር ሲነጻጸሩ የሰው ልጆች እንደ ገል መሆናቸው ተመልክቷል። እግዚአብሔር የሠራን ፈጣሪያችን ነው። እኛም የፍጥረቱ ሥራ ውጤቶች ነን። ይህንን ለመገዳደር መሞከር ማለት የፍጥረትን ሕግ ለመለወጥና የተፈጠርን ሰዎች ከፈጣሪ ጋር የመሟገት ብቃት እንዳለን ለማሳየት የሚደረግ ጥረት ነው።

<u>ሁለተኛ</u>፥ አንድ ልጅ ወደ አባቱና እናቱ ዞሮ ስለወለዱት ማጉረምረም እንደሌለበትም ኢሳይያስ የወላጆችንና ልጆችን የዝምድና ምሳሌ በማንሣት አብራርቶአል። ወላጆች ለልጆቻቸው የሚበጀውን የማድረግ መብት አላቸው። በተመሳሳይ ሁኔታ የአይሁዶች አባት የሆነው እግዚአብሔር ለልጆቹ በሚሆነው ነገር ላይ ሙሉ መብት አለው።

ስለሆነም ኢሳይያስ ለአይሁዶች የሚለው እንደተፈጠሩ ሰዎች ፈጣሪ አምላክን እንዳይገዳደሩትና ዓለምን የማስተዳደር መንገዱን

እንዳይጠይቁ ነው። ነገር ግን አንድ ቀን ወደ አገራቸው እንደሚመልሳቸውና ታላቅ ሕዝብ እንደሚያደርጋቸው የሰጠውን የተስፋ ቃል ተደግፈው በሰላም ሊኖሩ ይችላሉ።

25ኛ ጥያቄ፦ ሀ) አንዳንድ ጊዜ ክርስቲያኖች ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንገዶቹ የሚያማርሩባቸውን ሁኔታዎች ዘርዝር። ለ) ይህንን በሚያደርጉበት ጊዜ እግዚአብሔር በፈጣሪነትና በአባትነት ከእነርሱ ጋር ያለውን ዝምድና የሚዘነጉት እንዴት ነው?

4. እግዚአብሔር እስራኤልን የእጁ ሥራዎቹ የሆኑትን እስራኤላውያንን አንድ ቀን እንደገና ያንጻቸዋል (ኢሳ. 45፡11–13

ሁልጊዜም እግዚአብሔርን ለመገዳደር የምንነሣው እውቀታችን ውሱን ስለሆነ ነው። ከእኛ መሀል የእግዚአብሔርን የመጨረሻ የሥራ ውጤት የሚያውቅ ሰው ቢኖር ከቶውንም አናማርርም ነበር። ምክንያቱም የእግዚአብሔር መንገዶች ሁልጊዜም ለእኛ፥ ለቤተ ክርስቲያንና ለአገራችንም ከሁሉ የተሻሉ ናቸውና። ነገር ግን አንድ ክስተት በሚፈጸምበት ጊዜ በእግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ ምን እንዳለ አናውቅም። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር ወደ በኋላ ይገልጽልናል። ይሁንና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ በምናልፍበት ጊዜ አንድ ነገር ለምን እየተፈጸመ እንዳለ በአብዛኛው ምናባዊ ግንዛቤ እንኳ አይኖረንም። ለዚህ ነው ኢሳይያስ «በእውነት አንተ ራስህን የምትሰውር አምላክ ነህ» ለማለት የተገደደው (ኢሳ. 45፡15)።

የጥንቶቹ እስራኤላውያንም ሆኑ የዛሬዎቹ ክርስቲያኖች የእግዚአብሔር የእጁ ሥራዎች እንደመሆናችን ስለ እርሱ በምንናገረው ነገር ሁሉ ልንጠነቀቅ ይገባል። እግዚአብሔር ሰውን ጨምሮ የምድር ሁሉ ፈጣሪ ነው። ታላላቅ ሰማያትን የዘረጋና ሁሉንም የሚቆጣጠር አምላክ ነው። ስለሆነም ከፍጥረቶቹ የትኛውም አንድን ነገር የማድረግ መብቱን ሊቀናቀንበት አይገባም።

እግዚአብሔርን መገዳደር የማይኖርብን አንዱ ምክንያት የወደፊቱን ክስተቶች ስለማናውቅ ነው። እግዚአብሔር የሚሠራው ከየትኛው ውጤት ላይ ለመድረስ እንደሆነ አናውቅም። የምናውቀው ነገር ቢኖር የአሁኑን ሥቃይ ብቻ ነው። በምርኮኛነት እየተሠቃዩ የሚገኙ አይሁዶች ሊያዩት የሚችሉት ነገር ቢኖር የወቅቱን ሁኔታዎች ብቻ ነበር። ነገር ግን እግዚአብሔር በማጉተምተም ላይ ለነበሩት አይሁዶች በምሕረቱ ወደፊት ስለሚሆነው ነገር ገልጦላቸዋል። እንዲያውም እግዚአብሔር አይሁዶች ስለ ወደፊት እንዲጠይቁት አዞአቸዋል። ለዚህም ምክንያቱ ከእግዚአብሔር የታላቅነት ማረጋገጫዎች አንዱ ስለ

ወደፊት ክስተቶች ለመተንበይ መቻሉ እንደሆነ ስለሚታወቅ ነው። እግዚአብሔር ቂሮስን ያስነሣው ነበር። የቅጣትና የፍርድ ጊዜ አብቅቶ የዳግም ግንባታ ወቅት ስለተቃረበ ይህ ትክክለኛው ተግባር ነበር። እግዚአብሔር በምድር ላይ በቂሮስ አማካኝነት የሚፈጽማቸው ተግባራት ይከናወኑ ዘንድ መሰናክሎችን ሁሉ ያቃልል ነበር። በዚህ ዓይነት እግዚአብሔር በይሁዳ የወደመውን ነገር ሁሉ መልሶ ለመገንባት ቂሮስን በመሣሪያነት ይጠቀም ነበር። ከተሞቹ ዳግም ሊገነቡና አይሁዳውያን ምርኮኞች ተለቅቀው ወደ አገራቸው ይመለሱ ነበር። እግዚአብሔር ለባርነት ከሸጣቸው አይሁዶች ገንዘብ እንዳልተቀበለ ሁሉ፥ ቂሮስ ነጻነት ሰጥቷቸው ወደ አገራቸው እንዲመለሱ ሲያደርግም ገንዘብ አይከፍለውም ነበር።

5. እግዚአብሔር ሕዝቡንና የዓለምን ሕዝብ ሁሉ ያድናል (ኢሳ. 45፡14–25 አንብብ)

ሀ. እግዚአብሔር ሕዝቡን ያሳደዱትን ይቀጣል (ኢሳ. 45፡14)

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከዳር እስከ ዳር ከተጠቀሱት መርሆች አንዱ እግዚአብሔር የክፉ አድራጊዎችንና ሕዝቡን የሚያሳድዱትን ሰዎች ሁኔታ እንደሚቀለብስ ነው። እግዚአብሔር በዮሴፍ ሕይወት በመሥራት ዮሴፍን የሸጡት ወንድሞቹ እንዲሰግዱለት እንዳደረገ ሁሉ በአይሁዶች ላይ መከራን ያመጡት ሰዎችም የአክብሮት ስግደት ያቀርቡላቸዋል [መዝ. (68)፡31]። ኢሳይያስ በታሪክ ብዙ አይሁዶች ለባርነት የተሸጡባቸውን ሦስት ሩቅ አገሮች ጠቅሶአል። እነዚህም፥ ግብፅ፥ ኢትዮጵያ (በዕብራይስጡ መጽሐፍ ቅዱስ «ኩሽ» ተብላለች)፥ እና ሳባ ናቸው (ኢሳ. 43፡3)። የሳባ ምድር ከኢትዮጵያ ጎን በዛሬዋ የመንና ሰሜን ኢትዮጵያ ውስጥ ትገኝ ነበር። ምናልባትም እነዚህ አገሮች የሌሎችም አሕዛብ አገሮች ተምሳሌቶች በመሆን አንድ ቀን የእግዚአብሔር ሕዝብ በዓለም አገሮች ሁሉ ላይ የበላይነትን እንደሚቀዳጅ የሚያመለክቱ ይመስላል። እግዚአብሔር ሁኔታዎችን በሚቀለብስበት ወቅት አንድ ቀን ከኢየሩሳሌም የተወሰደው ንብረት ሁሉ ይመለሳል። ይህም የግብፅ፥ የኩሽና የሳባ ምርቶች ወደ ይሁዳ በሚመጡበት ጊዜ ተፈጻሚነትን ያገኛል። አንድ ቀን አይሁዶች ለባርነት የተወሰዱባቸው አገሮች ሁሉ ለአይሁዶች ይገዛሉ። ከሁሉም በላይ አይሁዶች ወደ ምርኮ በሄዱ ጊዜ አሕዛብ የአይሁዶችን አምላክ መሳለቂያ ማድረጋቸው ይታወቃል። አሁን ግን በአይሁዶች ፊት ለመዋረድ ስለሚገደዱ አማልክቶቻቸው ከንቱዎች እንደሆኑና የአይሁዶች አምላክ ብቻ እውነተኛ እንደሆነ በይፋ ይመሰክራሉ። አሕዛብ እስራኤላውያን ለአምላካቸው እንዲያማልዱአቸው ይጠይቃሉ።

በፊልጵስዩስ 2፡10 አንድ ቀን የዓለም ሁሉ ሁኔታ እንደሚለወጥ ተገልጾአል። የሚበዛው የዓለም ሕዝብ በኢየሱስ ክርስቶስ በማመን ጌትነቱን ለመቀበል ባይፈልግም፥ በምድር ላይ የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ ፊት ተንበርክከው የሚሰግዱበት ዘመን ይመጣል።

26ኛ ጥያቄ፡- እግዚአብሔርን የማይፈሩ ሰዎች በሚያሳድዱን ወቅት ይህ እውነት በእምነታችን እንድንጸና የሚረዳን እንዴት ነው?

ለ. የእግዚአብሔር መንገዶች ከሰው የተለዩ ናቸው (ኢሳ. 45፡15)

ኢሳይያስ ስለ እግዚአብሔር መንገዶች በሚያስብበት ጊዜ አብዛኛዎቹ የእግዚአብሔር መንገዶችና ዓላማዎች የተሰወሩ መሆናቸውን ለማመን ተገዶአል። ይህም እግዚአብሔር ራሱን ከሕዝቡ እንደሰወረ ያህል ነው። እንደ ዛሬው ሁሉ የዚያን ዘመኖቹም አይሁዶች፥ «እግዚአብሔር ሁሉን ቻይ አምላክ ከሆነ ኃጢአተኞቹን አጥፍቶ ችግር፥ መከራ፥ ወይም ክፉ ነገር በሌለበት አገዛዝ ሕዝቡን የማያከብረው ለምንድን ነው?» እያሉ መጠየቃቸው የማይቀር ነው። በታሪክ ሁሉ ሰዎች እግዚአብሔር የሚያደርገውን ነገር ለምን እንደሚያደርግ ለማወቅ ብዙ ጥረዋል። አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ታላላቅ ዓላማዎች የሚያመለክቱ ፍንጮችን እናያለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ደግሞ እግዚአብሔር በቸርነቱ እርሱን በእውነትና በመንፈስ ለመከተል የሚያስችል የፈቃዱን መገለጥ በበቂ ሁኔታ አኑሯል። በአጠቃላይ ግን እግዚአብሔር ከእኛ እንደተሰወረና መንገዶቹም ግልጽ እንዳልሆኑ መደምደም ይኖርብናል። ይህም በአውቃለሁ ባይነት እግዚአብሔር በአንድ ሁኔታ ውስጥ የሚያደርገውን ነገር እንዳንገምት ያስጠነቅቀናል። የእርሱ መንገዶች እኛ መቼም ከምንመርጣቸው መንገዶች የተለዩ ናቸው። ነገር ግን እግዚአብሔር በቸርነቱ በመከራ ጊዜ ከእርሱ ጋር ጸንተን እንኖር ዘንድ ስለ ነገሮች ፍጻሜ የሚበቃውን ሁሉ ገልጾልናል።

ሐ. አንድ ቀን በእግዚአብሔር ልጆችና በእግዚአብሔር ላይ በሚያምፁ ሰዎች መካከል በግልጽ የሚታይ ልዩነት ይከሰታል (ኢሳ. 45፡16-25 አንብብ)

1. እግዚብአሔር ጣዖት ሠሪዎችንና በጣዖታት ላይ የሚደገፉትን ሰዎች ያዋርዳል (ኢሳ. 45፡16)። በዚያን ጊዜ እጅግ ኃያል የሚመስሉ የዓለም ሃይማኖቶች የተሳሳቱ፥ ባዶዎችና ከንቱዎች መሆናቸው ይታወቃል። ዛሬ ከዓለም ሕዝብ 3/4ኛ ከጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የተለየ አምላክ ይከተላል። ብዙ ሰዎች ስለሚከተሏቸው እነዚህ ሃይማኖቶች ትክክል ይመስላሉ። ነገር ግን በሙስሊሞች፥ ቡድሂስቶች፥ ሂንዱዎችና

በሌሎችም የዓለም ሃይማኖቶች የሕዝብ ብዛት ልንሞኝ አይገባም። ቁምነገሩ እውነት ሲሆን፥ ይህም በመጨረሻው ዘመን የሚገለጽ ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ በሚመለስበት ጊዜ ሌሎች ሃይማኖቶች ሁሉ ከንቱነታቸው ተረጋግጦ ለውርደት ይጋለጣሉ። እነዚህን ሌሎች ሃይማኖቶች የሚከተሉ ሰዎች ኃፍረትና ፍርድ ይጠብቃቸዋል።

2. እግዚአብሔር ሕዝቡን እስራኤላውያንን ያድናል (ኢሳ. 45፥17)። የሐሰት ሃይማኖቶችን ከሚከተሉት በተቃራኒ፥ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ፍጹምና ሙሉ ደኅንነትን ያመጣላቸዋል። እግዚአብሔር ታላቅ አዳኝ እንደ መሆኑ፥ ሕዝቡን ከፖለቲካዊና ከመንፈሳዊ እስራቶች ነፃ ያወጣል። ይህም ለአይሁዶች ብቻ ሳይሆን ዛሬ በኢየሱስ ክርስቶስ አምነን የእግዚአብሔርን መንገድ የምንከተል ሰዎችን ሁሉ የሚጨምር ነው። ከማያምኑ ሰዎች በሚደርሱባቸው ስደቶችና በታማኝነት ባለመታዘዛቸው ሕዝበ እግዚአብሔር በታሪክ ሁሉ ለውርደት የተጋለጡ ቢሆኑም፥ ኃፍረታቸው ሁሉ ተወግዶ እንደ እግዚአብሔር ልጆች ለዘላለም የሚከበሩበት ዘመን ይመጣል።

3. እስራኤል የምትድን መሆኗ የእግዚአብሔር ዓላማና ባሕርይ አካል ነው (ኢሳ. 45፥18–19 ተመልከት)። ታሪክ ወዴት እያመራ ነው? እግዚአብሔር ለወደፊቱ ዘመን ምን ዕቅድ አለው? በዚህ ስፍራ ዝርዝር መግለጫ ባይቀርብልንም እግዚአብሔር ፍጹም ውድመት እንደማይመጣ ገልጾአል። እግዚአብሔር የፈጠረው ዓለም ሙሉ ለሙሉ ወድሞ ነዋሪ አልባ አይሆንም። ሕዝበ እግዚአብሔርም ሙሉ ለሙሉ አይደመሰሱም። ይልቁንም እግዚአብሔር መንግሥቱን በሰዎች ለመመሥላት ተግቶ ይሠራል።

እግዚአብሔር አንድ ቀን ለሕዝቡ ደኅንነትን የሚያመጣ መሆኑ ከባሕርዩ ውስጥ ተመልክቷል። እግዚአብሔር ሌላ ተወዳዳሪ የሌለው ብቸኛ ኃያል አምላክ ነው። እንዲሁም እግዚአብሔር ከዕቅዶቹ ውስጥ የሚበቃውን ያህል ስለገለጠ ሊከተሉት ለሚወዱ ሁሉ የወደፊቱ ጎዳና ጥርት ብሎ የሚታይ ነው። እግዚአብሔር ቃሉን እንደ ኢሳይያስ ባሉት ነቢያት ስለተናገረና ትንቢቶቹን ለወደፊት ትውልድ በጽሑፍ ስላስቀመጠ አንድ ቀን የሚከሰተው ነገር ለሁሉም በግልጽ ተቀምጦአል። እግዚአብሔር ዓላማዎቹን በጨለማ ውስጥ አልደበቃቸውም፤ ከሰዎች ደብቆ ለተወሰኑ ምርጦች ብቻ በምሥጢራዊ መንገዶች አላሳያቸውም። ይልቁንም ለሰዎች ሁሉ በግልጽ ተናግሯል። እግዚአብሔር ሊዋሽ ስለማይችል የወደፊት ትንቢቶቹ በትክክል ይፈጸማሉ። ጽልመት ነግሦ ተስፋ የመከነ በሚመስልበት ወቅት ሳይቀር እስራኤላውያን ከአንጀታቸው ቆርጠው እግዚአብሔርን ሊከተሉ

ይገባል። አንድ ቀን እግዚአብሔር በዓለም ውስጥ ያሉትን ነገሮች በመቀልበስ እስራኤልን ይሸልማታልና።

27ኛ ጥያቄ፡– መከራና ስደት በበዛባቸው የጨለማ ጊዜያት ስናልፍ ይህ መርህ ለእኛም እውነት የሚሆነው እንዴት ነው? እግዚአብሔር ቃል የገባልንን ሽልማት እናገኝ ዘንድ እስከ መጨረሻው ታማኞች ሆነን መገኘት የሚኖርብን እንዴት ነው?

4. እግዚአብሔር እርሱ ብቻ አምላክ እንደሆነ ሕዝቡ እንዲገነዘቡ ያስጠነቅቃል (ኢሳ. 45፡20–21)። ኢሳይያስ ቀደም ባሉት አምስት ምዕራፎች አያሌ ጊዜያት እንደደጋገመው፥ አሁንም የአሕዛብን አማልክተ ጣዖታት ይገዳደራቸዋል። ከአሕዛብ ያመለጡ ሁሉ እንዲሰበሰቡ ያዛል። እነዚህ «ያመለጣችሁ» የተባሉት በቂሮስ ዘመን ከሚመጣው ታላቅ ውድመት የሚተርፉ ሳይሆኑ አይቀሩም። (ይህ ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ በዓለም ላይ የሚደርሰውን ፍርድ በተምሳሌትነት የሚያሳይ ሲሆን፥ ያንን ታላቅ የፍርድ ቀን የሚያመልጡትን ያመለክታል።) ወይም ደግሞ እነዚህ የጣዖታትን ከንቱነትና እግዚአብሔር በጣዖት አምላኪዎች ላይ የሚያመጣውን ፍርድ ተገንዝበው ወደ እግዚአብሔር የሚመለሱ ሊሆኑ ይችላሉ። ከጦርነት የሚሸሹ ሰዎች በስደተኝነት ወግ ከአንድ አገር ወደ ሌላ አገር ይወሰዳሉ። እግዚአብሔር ለረዥም ጊዜ የተማመኑባቸውን አማልክት ይዘው ከፊቱ እንዲቀርቡ ያዛል። እነዚህ አማልክት የቂሮስን መምጣት እንዴት እንደተነበዩ እንዲያሳዩ ተጠይቀዋል። አማልክቱ ሊተነብዩ ባለመቻላቸው ዝም ብለው ተቀምጠዋል። የቂሮስን መምጣት አስቀድሞ በመተንበይ ልዩ፥ ኃያል፥ የሕዝቡ አዳኝና በምድር ላይ ትክክለኛውን ነገር የሚያደርግ ብቸኛ አምላክ መሆኑን ያስመሰከረው እግዚአብሔር ብቻ ነበር። በጣዖታት ላይ መደገፋቸውን የቀጠሉት ሰዎች ሊያድናቸውና ሊሰማቸው በማይችል ነገር ስለተማመኑ አላዋቂዎች ሆነዋል።

5. እግዚአብሔር የዓለም ሕዝብ ወደ እርሱ ተመልሰው እንዲድኑ ይጋብዛል (ኢሳ. 45፡22–25)። ዛሬ ብዙዎች ክርስቲያኖች እንደሚያደርጉት ብዙ አይሁዶች የእግዚአብሔር ማዳንና በረከት ለተመረጡት ጥቂት ወገኖች ብቻ እንደሚደርስ የማሰብ አዝማሚያ ይታይባቸው ነበር። አይሁዶች እነርሱ ምርጥ ሕዝብ በመሆናቸው እግዚአብሔር ለሌሎቹ የዓለም ሕዝብ እንደማይገደው ያስቡ ነበር። ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ በነበረበት ወቅት አይሁዶች አሕዛብ ለጥፋት ስለተፈጠሩ ደኅንነትን ሊያገኙ እንደማይችሉ ያስቡ ነበር። ዛሬ ግን ደኅንነት ለሰዎች ሁሉ እንደተሰጠ ስለምናውቅ በዚህ ጉዳይ ላይ እንደማንከራከር ግልጽ ነው። ይሁንና፥ ለተወሰኑ ጎሳዎች

ወይም ስደተኞች፥ ብረታ ብረት ቀጥቃጮችና ሸክላ ሠሪዎች ለመሳሰሉ ማኅበራዊ ቡድኖች ወንጌልን አለመስበካችንና ከሌሎች ጋር በእኩልነት ወደ ቤተ ክርስቲያን እንዲመጡ አለማድረጋችን ደኅንነት ለሰዎች ሁሉ እንደተሰጠ አለማመናችንን ያሳያል።

እግዚአብሔር ግን የሰዎች ሁሉ አምላክ እንደመሆኑ አድልዎን አያሳይም (የሐዋ. 10፡34–35፤ ሮሜ 2፡1–11)። ስለሆነም እንደ አይሁዶቹ ሁሉ በበረከቱ ደስ ይሰኙ ዘንድ አሕዛብን ይጋብዛል። ወደ እርሱ ተመልሰው ደኅንነትን ሊያገኙ ይገባ ነበር። እንደ አይሁዶቹ ሁሉ በዓለም ላይ አንድ ፈጣሪ አምላክ ብቻ እንዳለ ማወቅ ያስፈልጋቸው ነበር። አንዱ አምላክ ሰዎች ሁሉ ስለ ማንነቱና ከእርሱ ጋር ግንኙነት ሊፈጥሩ ስለሚችሉበት ሁኔታ እንዲገነዘቡ ይሻል። ይህ በጣም አስፈላጊ ነጥብ በመሆኑ እግዚአብሔር የደኅንነት ተስፋውን በመሀላ ያጠናክራል።

28ኛ ጥያቄ፡– ዕብራውያን 6፡13 አንብብ። ሀ) እግዚአብሔር የተስፋ ቃሉን በመሀላ የሚያጠናክረው ለምንድን ነው? ለ) ይህ እውነት ለእግዚአብሔር በጣም አስፈላጊ ስለመሆኑ ምን መልእክት ያስተላልፍልናል?

ሰዎች ቃል ኪዳን በሚገቡበት ጊዜ የተነጋገሩት ነገር እውነት መሆኑን ለማጠናከር ብዙውን ጊዜ ከእነርሱ የላቀውን አካል ስም ይጠራሉ። በንጉሡ ጊዜ የነበሩት ሰዎች እውነት መናገራቸውን ለማረጋገጥ፥ «ኃይለ ሥላሴ ይሙት!» ይሉ ነበር። እግዚአብሔር ግን ከእርሱ የበለጠ ማንም ስለሌለ በራሱ ስም ይምላል።

እግዚአብሔር በትክክል እንደሚፈጸም የ ተናገረው አሳብ ምን ነበር? እግዚአብሔር ሁለት ነገሮች እንደሚከሰቱ ምኗል። <u>በመጀመሪያ</u>፥ አንድ ቀን በምድር ላይ የሚገኘው ጉልበት ሁሉ ለእርሱ ይንበረከካል ብኗል። መንበርከክ የአክብሮት ምልክት ብቻ ሳይሆን ዝቅ የማለትና የአገልጋይነትም ምልክት ነበር። አንድ ሰው በንጉሥ ፊት ሲንበረከክ የንጉሡን ታላቅነት በመገንዘብ ራሱን ዝቅ ማድረጉና ትእዛዛቱን ለመፈጸም ዝግጁ መሆኑን መገንዘቡ ነው። በተጨማሪም መንበርከክ የአምልኮ ምልክት ነው። ዛሬ አብዛኛው የዓለም ሕዝብ በፈቃዱ መንፈሳዊ ጉልበቱን ለእግዚአብሔር ለማንበርከክ አልፈለገም። ሕይወታቸው በራሳቸው መንገድ በሚያደርጉት መሯሯጥ የተሞላ ነው። እግዚአብሔርን በሕይወታቸው ላይ ከማንገሥ ይልቅ ራሳቸው በሕይወታቸው ላይ ለመንገሥ ይፈልጋሉ። ይህ ግን ሁልጊዜ እንዲህ አይሆንም። አንድ ቀን የምድር ላይ ነዋሪዎችና የሰው ዘር የተባለው ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት ይንበረከካል። እግዚአብሔር ከአዳም ጀምሮ እስከ መጨረሻው ሰው

ድረስ የጌትነት መብቱን ያላወቀውን ማንንም ቢሆን አለፍርድ አይተወውም። ሂትለሮች፥ ሞሶሎኒዎች፥ ስታሊኖች፥ ክሊንተኖችና መንግሥቱዎች ጉልበቶቻቸውን ለእግዚአብሔር ያንበረከካሉ።

ሁለተኛ፥ በሌሎች ሃይማኖቶች ወይም ጣዖታት ሳይሆን በእግዚአብሔር ብቻ ጽድቅ እንደሚገኝ ሰዎች ይገነዘባሉ። ፍትሕ የሚገኘው በእግዚአብሔር ብቻ ነው። የዓለም ክፋት ሁሉ ወደ ትክክለኛነት የሚለወጠው በእግዚአብሔር ብቻ ነው። እግዚአብሔር ያደረገውና የሚያደርገው፥ በታሪክ ሁሉ ያከናወነው ተግባር ትክክለኛ መሆኑ ይረጋገጣል። እግዚአብሔር ፍትሐዊ እንዳልሆነ በመጥቀስ የሚቀርብ ማጉተምተም አይኖርም። በተጨማሪም ሰዎች ኃይል በእግዚአብሔር ብቻ እንደሚገኝ ያምናሉ። የአማልክቶቻቸውና የሐሰተኛ ሃይማኖታቸውን እንዲሁም የሠራዊታቸውንና የጦር መሣሪያዎቻቸውን ደካማነት ያውቃሉ። እግዚአብሔር ኃያልና ሉዓላዊ የአጽናፈ-ዓለሙ ንጉሥ እንደሆነ ይገነዘባሉ። እግዚአብሔር በእነርሱ ላይ የነበረውን ትክክለኛ ሥልጣን ሲጋፉ በመቆየታቸው ስሕተት መፈጸማቸውን ይረዳሉ። ታላላቅ ነገሥታትም ሳይቀር የእግዚአብሔርን ሁሉን ቻይነት ለመቀበል ይገደዳሉ።

ሁሉ የእግዚአብሔርን ጽድቅና ብርታት በማመን ጉልበታቸውን ቢያንበረክኩም እነዚህ ሰዎች ለሁለት ይከፈላሉ። በመጀመሪያ፥ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ በእግዚአብሔር ላይ ሲያምፁ የኖሩ ሰዎች አሉ። እነዚህ ሰዎች በእግዚአብሔር ፊት የሚንበረከኩት እና ታላቅነቱን የሚመሰክሩት በፈቃዳቸው ሳይሆን የእግዚአብሔር ኃይል ዝቅ እንዲሉ ስለሚያስገድዳቸው ነው። በዚያን ቀን ትዕቢተኛ ሰው አይኖርም፤ ያለፈውንም በደል የመናዘዝ ዕድል አይገኝም። ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ ሊነግሥ በሚመጣበት ጊዜ ንስሐ የመግባትና የመለወጥ ዕድል ያከትማል። ወደ ዘላለማዊ ፍርድ በሚላኩበት ወቅት የሚቀረው ኃፍረት ብቻ ይሆናል።

29ኛ ጥያቄ፡- ማቴዎስ 25፡31-46፤ ራእይ 20፡11-15 አንብብ። ከዚህ ንባብ በኃጢአተኞች ላይ ስለሚደርስ ፍርድና ስለሚጠብቃቸው ዕድል ምን ትማራለህ?

ሁለተኛ፥ በምድር ላይ በነበሩበት ወቅት ጉልበቶቻቸውን ለእግዚአብሔር ያንበረከኩ የእግዚአብሔር ልጆች ይኖራሉ። ለእነርሱ በመጨረሻው ዘመን ጉልበቶቻቸውን ለእግዚአብሔር ማንበርከኩ ከባድ አይሆንም። እንዲያውም በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ ራሳቸውን አዋርደው ለንጉሡ ሲሰግዱ ስለኖሩ ይህ ተፈጥሯዊ ልማዳቸው ሆኗል። ዕለት በዕለት መንፈሳዊ ስግደት ሲፈጽሙ ኖረዋል። ስለሆነም፥ መስገዱ ለእነርሱ አዳጋች ጉዳይ አይሆንም። ኢሳይያስ እንዳለው፥

ሕይወታቸውን በእግዚአብሔር ዓላማና ፈቃድ ስለኖሩ በእግዚአብሔር ፊት ጻድቃን ሆነው ይገኛሉ። እነዚህ ጻድቃን በምድር ላይ ሆነው ጉልበቶቻቸውን ለእግዚአብሔር ለማስገዛት ካልፈለጉት ሰዎች ብዙ ኃፍረትና ሥቃይ ተቀብለው ሊሆን ይችላል። በዚያን ጊዜ ግን ይከብራሉ። ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር የመኖር ደስታ ሲገጥማቸው በምድር ላይ ለጊዜው እንደ እንግዶች የኖሩበት ኃፍረት ይለቃቸዋል (1ኛ ጴጥ. 1፡17፤ 2፡11–12፤ በተለይ 2ኛ ቆሮ. 4፡16–18 ተመልከት)።

30ኛ ጥያቄ፡– ሀ) በምድር ላይ በአብዛኛው የጻድቁና የኃጢአተኛው ዕጣ ፈንታ ምን እንደሚመስል አነጻጽረህ ግለጽ። ብዙውን ጊዜ የሚዋረደው ማን ነው? የሚከብረውስ? ለ) በመጨረሻው ዘመን የጻድቁና የኃጢአተኛው ዕጣ ፈንታ ምን እንደሚመስል አነጻጽር። ሐ) ይህ አሁን ክብርን መርጦ በኋላ ኃፍረትን ከመጋፈጥ፥ አሁን ኃፍረትን መርጦ በኋላ በክብር ደስ የመሰኘቱን አስፈላጊነት የሚያሳየው እንዴት ነው?

31ኛ ጥያቄ፡– በኢሳይያስ ምዕራፍ 45 የተመለከትሃቸውና በቤተ ክርስቲያንህ ውስጥ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ሊሰጡ የሚገባቸው ትምህርቶች ምንድን ናቸው?

አራተኛ ቀን፤ የዚህን ሳምንት ትምህርት ከልስና ለሳምንታዊ ውይይት ተዘጋጅ።

ሳምንታዊ ስብሰባ

1. ሀ) ከኢሳይያስ 43–44 እግዚአብሔር ከአይሁዶች ጋር ያለውን ግንኙነት የገለጸው እንዴት ነው? ለ) ይህ ዛሬ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ከሚያደርገው ግንኙነት ጋር የሚመሳሰለው እንዴት ነው? ሐ) በኃጢአት በሚወድቁበት ጊዜ የሚሆነውን ሁኔታ ጨምሮ በተለይም በአስቸጋሪ ሁኔታዎች ወቅት ለክርስቲያኖች የእግዚአብሔርንና የሕዝቡን ግንኙነት መረዳቱ አስፈላጊ የሚሆነው እንዴት ነው?

2. ሀ) ከኢሳይያስ 43–45 እውነተኛ አምላክ በሰው እጅ ከተሠሩት ጣዖታትና አማልክት ጋር የተነጻጸረው እንዴት ነው? ለ) እግዚአብሔር ለአይሁዶች እርሱ ከየትኛውም በሰው እጅ ከተሠራ ጣዖት በላይ እንደሆነ ያሳየው እንዴት ነበር? ሐ) ዛሬ ኢትዮጵያውያን የሚከተሏቸው አንዳንድ አማልክት (ጣዖታት፥ ፍልስፍናዎች፥ አሳቦች) ምንድን ናቸው? መ) እነዚህ ሁሉ የሰዎች ፈጠራዎች የሆኑት እንዴት ነው? ሠ) ብዙ ክርስቲያኖች እነዚህን አማልክት ለመከተል የሚፈተኑት እንዴት ነው? ረ) የቤተ ክርስቲያን መሪዎች የሐሰተኛ አስተሳሰቦች፥ ፍልስፍናዎች ወይም አማልክት አደገኛነትን ምእመኖቻቸው እንዲገነዘቡ ለማድረግ ምን ሊሠሩ ይገባል? ሰ) ስለ እግዚአብሔር

የተሳሳተ አስተሳሰብ እንዳይኖረን ትክክለኛ ማንነቱን ጥርት አድርጎ ማወቅ የሚጠቅመው እንዴት ነው?

3. ሀ) ከኢሳይያስ 43–45 ስለ አይሁዶች የተሰጡት ትንቢቶች ምንድን ናቸው? ከእነዚህ ትንቢቶች አንዳንዶቹ የተፈጸሙት እንዴት ነው? ለ) ስለ መጨረሻው ዘመን የተሰጡት ትንቢቶች ምንድን ናቸው? ሐ) ስለ ትንቢት ከሚነገሩት ሦስት አመለካከቶች እነዚህ ትንቢቶች ሊፈጸሙ የሚችሉባቸው መንገዶች የትኞቹ ናቸው? መ) የትኛውን አመለካከት ትደግፋለህ? ለምን?

4. ሀ) ስለ ቂሮስ የተነገሩትን የተለያዩ ትንቢቶች ዘርዝር። ለ) ከዚህ ትምህርት እግዚአብሔር ከዓለም መሪዎች ጋር ስላለው ግንኙነት ምን እንማራለን? ሐ) በዓለም መሪዎችና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ግልጽ ግንኙነት በመረዳት ክርስቲያኖች ሊያገኙት የሚችሉት ማጽናኛ ምንድን ነው?